# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
## የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

### አንደኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን ሙስጌታ

ግንቦት
፳፻፮ ዓ.ም

www.zeorthodox.org

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፮ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት

__አድራሻ__:-
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- kesisolomon@gmail.com
Website፡- www.zeorthodox.org

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው

www.zeorthodox.org

# ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ፡፡ በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም፡፡

# መታሰቢያነቱ



በጥር ወር ፲፱፻፺ ዓ.ም. በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሙሉ ድምጽ ለጵጵስና ታጭተው ይህን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ከቅዱስ ሲኖዶስ ሲደርሳቸው ‹‹… እንኳንስ አቅሜ የማይፈቅደውንና ከአቅሜ በላይ የሆነውን ማዕረገ ጵጵስና ቀርቶ የደብር አስተዳዳሪነቱም ይበዛብኛል… ለዚህም ክብር የማልበቃ ምስኪን ሰው ነኝ…›› ብለው ምላሽ በመስጠት ወደ ላይ ከመሻት ይልቅ በተቀበሉት ሥልጣነ ክህነትና በተሸከሙት መስቀል በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ አባታዊ አቋማቸው ሳይለዋወጥ ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊና መንፈሳዊ አገልግሎት መቃናት ለደከሙ፣ ለታሰሩ፣ ለተገረፉና፣ ለተሰደዱ አሁን ዐረፍተ ዘመን ለገታቸው ለመልአከ ገነት አባ ኃይለማርያም አብርሃም ይሁንልኝ፡፡

# ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል፡፡

# ማውጫ


| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ | 1 | | አንደኛ | |
| 2. | አዳም በገነት ውስጥ | 3 | | ሁለተኛ | |
| 3. | እግዚአብሔር ሔዋንን ፈጠረ | 5 | | ሦስተኛ | |
| 4. | ፈታኙ እባብ | 7 | | አራተኛ | |
| 5. | ኖህ | 9 | | አምስተኛ | |
| 6. | ኖህና መርከቡ | 11 | | ስድስተኛ | |
| 7. | እንዴት እንጸልይ? | 13 | | ሰባተኛ | |
| 8. | ዳዊትና ዮናታን | 15 | | ስምንተኛ | |
| 9. | መረቤን በዓሣ ሞላ | 17 | | ዘጠነኛ | |
| 10 | ኢየሱስ በቤተ ሳይዳ የሚኖረውን ሕመምተኛ ፈወሰ | 19 | | ዐሥረኛ | |
| 11. | ሶምሶንና አንበሳው | 21 | | ዐሥራ አንደኛ | |
| 12. | ሶምሶን ኃይሉን አጣ | 23 | | ዐሥራ ሁለተኛ | |
| 13. | ቅዱስ ገብርኤል እና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም | 25 | | ዐሥራ ሦስተኛ | |
| 14. | እረኞችና መላእክት | 27 | | ዐሥራ አራተኛ | |
| 15. | አናጢው ቅዱስ ዮሴፍ | 29 | | ዐሥራ አምስተኛ | |
| 16. | ጦቢት እና መልአኩ | 31 | | ዐሥራ ስድስተኛ | |
| 17. | ነቢዩ ኤልሳዕና የመላእክት ጥበቃ | 33 | | ዐሥራ ሰባተኛ | |
| 18. | ነቢዩ ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ | 35 | | ዐሥራ ስምንተኛ | |
| 19. | ነቢዩ ዮናስ እና ቅሉ | 37 | | ዐሥራ ዘጠነኛ | |
| 20. | ሕፃኑ ሳሙኤል | 39 | | ሃያኛ | |
| 21. | ቅዱስ መስቀል | 41 | | ሃያ አንደኛ | |
| 22. | እረኛው ዳዊት | 43 | | ሃያ ሁለተኛ | |
| 23. | የዳዊት ለንጉሥነት መብቃት | 45 | | ሃያ ሦስተኛ | |
| 24. | የጠፋው በግ | 47 | | ሃያ አራተኛ | |
| 25. | ኢየሱስ ዐይነ ስውሩን አበራ | 49 | | ሃያ አምስተኛ | |
| 26. | ልጆች ክርስቶስን ተቀበሉ | 51 | | ሃያ ስድስተኛ | |
| 27. | መልአኩ የመቃብሩን ድንጋይ አንከባለለ | 53 | | ሃያ ሰባተኛ | |


www.zeorthodox.org

| ተ. ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 28. | ዮርዳኖስን ተሻገሩ | 55 | | ሃያ ስምንተኛ | |
| 29. | ቅዱስ ጴጥሮስ ጣቢታን አስነሣ | 57 | | ሃያ ዘጠነኛ | |
| 30. | በዐለት ላይ የተሠራ ቤት | 59 | | ሠላሳኛ | |
| 31. | አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ | 61 | | ሠላሳ አንደኛ | |
| 32. | የመክሊት ምሳሌ | 63 | | ሠላሳ ሁለተኛ | |
| 33. | የእርሻው ምሳሌ | 65 | | ሠላሳ ሦስተኛ | |
| 34. | አራት ሰዎች ሽባውን መሸከማቸው | 67 | | ሠላሳ አራተኛ | |
| 35. | የአስቴር ንግሥት መሆን | 69 | | ሠላሳ አምስተኛ | |
| 36. | የአስቴር ጥንካሬ | 71 | | ሠላሳ ስድስተኛ | |
| 37. | ደጓ ሩት | 74 | | ሠላሳ ሰባተኛ | |
| 38. | በለዓምና አህያው | 76 | | ሠላሳ ስምንተኛ | |
| 39. | የእመቤታችን የማርያም ልደት | 78 | | ሠላሳ ዘጠነኛ | |
| 40. | የቤተ ክርስቲያን ፍቅር | 80 | | ዐርባኛ | |
| 41. | መልአኩ ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር ቤት ነጻ አወጣው | 82 | | ዐርባ አንደኛ | |
| 42. | እናትና አባትን ማክበር | 84 | | ዐርባ ሁለተኛ | |
| 43. | የእግዚአብሔር ፍቅር | 86 | | ዐርባ ሦስተኛ | |
| 44. | መታዘዝ | 88 | | ዐርባ አራተኛ | |
| 45. | ታማኝ መሆን | 90 | | ዐርባ አምስተኛ | |
| 46. | የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ማክበር | 92 | | ዐርባ ስድስተኛ | |
| 47. | ቅዱስ ቁርባንን መቀበል | 94 | | ዐርባ ሰባተኛ | |
| 48. | በጸሎት ማደግ | 96 | | ዐርባ ስምንተኛ | |

www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል፡፡

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሥራብት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ፡፡ ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ፡፡ አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

www.zeorthodox.org

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሯል። በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ።

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለኅትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ።

***“እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል።” ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው። በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል።

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል። በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሚያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል። ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው።

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው። ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ። በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ።

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም። በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣ ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል

www.zeorthodox.org

ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሲዘምሩላቸውና ሲያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኀበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

በመጨረሻም ይኸን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

# እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ መሆኑን በማስረዳት ፍጥረታት ለእግዚአብሔር ክብርና ለእኛ ጥቅም መፈጠራቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር የፈጠረው መልካም እንደሆነ አየ፡፡" ዘፍ.፩÷፴፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ኦሪት ዘፍ. ፩ እና ፪፤ ኢሳ. ፵፬÷፳፤ ኤር. ፶፩÷፲፭ እና ዮሐ. ፩÷፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- የአበቦች፣ የድንጋዮች፣ የፍራፍሬዎችና የእንስሳት ሥዕል በማቅረብ፤ ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ተፈጥሮን እንዲጎበኙ በማድረግ የእግዚአብሔርን ፍጥረታት እንዲያውቁ ያስተምራቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ነው፡፡ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ፡፡ ምድር ባዶዋን ነበረች፡ አንዳች ነገር አልነበረባትም፡፡ ዛፎች፣ ቤቶች፣ መኪኖች፣ እንስሳትና ሰዎች አልነበ ሩባትም፡፡ ጨለማም በላይዋ ተጋርዶ ነበር፡፡

እግዚአብሔር፤ "ሰውን እፈጥራለሁ፤ ስሙንም አዳም ብዬ እጠራዋለሁ፤ ደስተኛ እንዲሆን እፈልጋለሁ፡፡ እንዲወደኝና በማንኛውም ጊዜ እንዲጠራኝ እሻለሁ፡፡ ስለዚህ ሁሉን ነገር ለእርሱ ምቹ አድርጌ ልፍጠረው፡፡ ጨለማ እንዳይጋርደው ብርሃንን ልፍጠርለት" አለ፡፡ "ብርሃን ይሁን" ብሎ በቃሉ ሲናገር ብርሃን ተፈጠረ፡፡ ምድርም ለመጀመሪያ ጊዜ የብርሃንን ገጽ ለማየት ቻለች፡፡

እግዚአብሔር ብርሃኑን ቀን፤ ጨለማውን ሌሊት ብሎ ጠራው፡፡ አዳም ቀን ቀን እንዲሠራ፤ ሌሊት ሌሊት ደግሞ እንዲያርፍ ፈቀደለት፡፡ እግዚአብሔር በሌሊት ሰማይን የሚያስውቡ ከዋክብትን፤ የሌሊቱን ጨለማ አሸንፋ ብርሃን የምትለግሰን ጨረቃን፤ በቀን ፍጥረትን የምታሞቅ ፀሐይን ፈጠረ፡፡

እግዚአብሔር ለሰው ምግቡን ከነፍላጎቱ ፈጥሮለታል፡፡ አትክልት፣ አዝርዕት፣ ዕፀዋት፣ ፍራፍሬዎችና እንስሳት ለእኛ ጥቅም ምግብ እንዲሆኑ ተፈጥረዋል፡፡

አዳም ሲጠማው የሚጠጣው፤ ሲቆሽሽ የሚታጠብበትና ምግብ የሚሠራበት ውኃን እግዚአብሔር ፈጠረ፡፡ እግዚአብሔር



www.zeorthodox.org

በክንፍ የሚበሩ አእዋፍን፣ በእግር የሚሄዱ እንስሳትን፣ በደረታቸው የሚሳቡ ነፍሳትን፣ በየብስና በባሕር በሰማይና በምድር የሚኖሩ ፍጥረታትን ሁሉ ከፈጠረ በኋላ በስድስተኛው ቀን ሰውን ፈጠረ፤ ስሙንም አዳም ብሎ ጠራው፡፡ አዳም አምላኩን በመልክ የሚመስል ብቸኛ ፍጡር ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ፤ ያም ቀን ሰንበት ተባለ፡፡

## ማጠቃለያ

ሕፃናት እግዚአብሔር የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ነው፡፡ ፍጥረታትን በስድስት ቀናት ፈጥሮአል፡፡ ሁሉን አስውቦ ምቹ ሁኔታዎችን አዘጋጅቶ ሰውን ፈጠረ፡፡ ሰውንም አዳም ብሎ ጠራው፡፡ እግዚአብሔር ለአዳም የነበረውን ጽኑ ፍቅር በሥራው አሳየ፡፡ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ከፈጸመ በኋላ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ፡፡ ያም ቀን ሰንበት ተብሏል፡፡ እግዚአብሔር እንዲወደን በስድስቱ ቀናት ሥራችንን ሠርተን በሰንበት ማረፍ አለብን፡፡

## ጥያቄዎች

፩. ልጆች የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ማን ነው?

፪. እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው ምንድን ነው?

፫. እግዚአብሔር በስንት ቀናት ፍጥረታትን ፈጠረ?

፬. እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ ማን ብሎ ጠራው?

፭. እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለምን ፈጠረ?

## ተግባር

መምህሩ ሕፃናት የተለያዩ አበቦችን፣ ቢራቢሮዎችን፣ ወፎችን፣ የቤትና የዱር እንስሳትን እንዲሥሉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# አዳም በገነት ውስጥ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ጽኑ ፍቅር፤ ፍቅሩንም ለመግለጽ የሚያደርገውን ጥበቃና እንክብካቤ ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር" ዘፍ.፩÷፳፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፪÷፰-፳፫፣ መዝ. ፰÷፩-፮

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- አዳምን የሚጠቅሙትን ፍጥረታት እንዲዘረዝሩ ይጠይቃቸው፡፡
- ስለ ገነት መጠነኛ እውቀት እንዲኖራቸው በሥዕል የተደገፈ ማብራሪያ ይስጣቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ገነት ለማየት ደስ በሚያሰኙ፤ ለመብላት መልካም በሆኑ ዛፎች የተሞላች፤ በአራት ወንዞች የተከበበች ውብ ስፍራ ናት፡፡ ውብ በነበረችው ኤደን ገነት አዳም ምንም ሳይጎድልበት መኖር ጀመረ፡፡ አዳም በማንኛውም ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገር ነበር፡፡ እግዚአብሔርም አዳምን "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና" አለው፡፡

አንድ ቀን እግዚአብሔር እንስሳትን ሁሉ ወደ አዳም አመጣቸው፤ አዳምም ባያቸው ጊዜ ደስ አለው፡፡ ከእነርሱም ጋር መጫወት ጀመረ፡፡ እግዚአብሔርም "ስም አውጣላቸው" አለው፡፡ አዳምም ሕያው ነፍስ ላላቸው ሁሉ ስም አወጣላቸው፡፡

አዳም ስለሁሉም ነገር አምላኩን እግዚአብሔርን አመሰገነ፡፡ አዳም ሁሉንም ፍጥረታት ሲያይ እርሱን የሚመስል አላየም፡፡ እግዚአብሔርም የአዳምን ብቸኝነት አየ፡፡ ለአዳም ረዳት፣ ጓደኛና እኅት የምትሆነው ሔዋንን ፈጠረለት፡፡ በቀጣዩ ክፍለ ትምህርታችን እግዚአብሔር ሔዋንን እንዴት እንደፈጠራት እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር አዳምን በውብ ገነት አስቀመጠው፤ በሁሉ እንስሳት ላይ የገዢነት ሥልጣን ሰጠው፡፡ ሁሉም ፍጥረታት ከአዳም ጋር በሰላምና በመታመን ተገዝተውለት ይኖሩ ነበር፡፡ አዳምም ይንከባከባቸው ነበር፡፡ ለእያንዳንዳቸውም ስም አወጣላቸው፡፡

### ጥያቄዎች፡-

፩. አዳም በየት ይኖር ነበር?

፪. እግዚአብሔር ለአዳም ምን ትእዛዝ ሰጠው?

፫. ለእንስሳት ስም ያወጣላቸው ማን ነበር?

## ተግባር፡-

መምህሩ ሕፃናት የሚወዷቸውን እንስሳት ሥለው እንዲያሳዩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# እግዚአብሔር ሔዋንን ፈጠረ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ሔዋንን እንዴት እንደፈጠራት ማስገንዘብ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" ዘፍ.፪÷፲፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፪÷፲፰-፳፬፣ ማቴ. ፲፱÷፭-፮ እና ኤፌ. ፭÷፴፩-፴፫

## መግቢያ

❧መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡

❧የሔዋንን ሥዕል አዘጋጅቶ ለልጆች ያሳያቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር አዳምን ግሩምና ድንቅ አድርጎ ፈጥሮ በገነት አኖረው፡፡ አዳምም በገነት ብቻውን መኖር ጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ግን የአዳም ብቸኝነት መልካም እንዳልሆነ አየ፡፡ ስለዚህ "የምትመቸውን ረዳት እንፍጠርለት" አለ፡፡

አዳም እንስሳትን ካየ በኋላ እርሱን የሚመስል ብቸኝነቱን የሚያርቅለት ፍጡር በማጣቱ ተገርሞ ሳለ እንቅልፍ ወስዶት ተኛ፡፡ እግዚአብሔርም ከአዳም ጎን አንዲት አጥንት ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው፡፡ ከአዳም የወሰደውን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት፡፡

አዳም ባያት ጊዜ ተገረመ፤ ደስተኛ ሆነ፡፡ "ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፣ ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል" አለ፡፡ አዳም ከረዳቱ ከሔዋን ጋር በአረንጓዴዋ ገነት አብሮ በደስታ መኖር ቻለ፡፡

## ማጠቃለያ

አዳም ብቻውን እንዲኖር ፈቃዱ ያልሆነ እግዚአብሔር ሔዋን የምትባል ረዳት ፈጠረለት፡፡ ሕፃናት እግዚአብሔር ለሰው የሚያስብና ሰው የሚያስፈልገውን ሁሉ ያሟላ አምላክ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች***

፩. እግዚአብሔር ሔዋንን ለምን ፈጠረ?

፪. እግዚአብሔር ሔዋንን እንዴት ፈጠራት?

፫. የአዳምና የሔዋን ፈጣሪ ማን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ አዳምና ሔዋን በገነት ጫካዎች ሲጫወቱ የሚያሳይ ሥዕል ያሥላቸው፡፡
- በቃል የሚጠናውን ጥቅስ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ፈታኙ እባብ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች እግዚአብሔርን እንዲሰሙ፣ ትእዛዙንም እንዲጠብቁና በመታመን በፊቱ እንዲያድጉ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አዳም መልካምንና ክፉውን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ" ዘፍ.፫÷፳፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ.፫÷፩-፲፫፣ ራእ.፲፪÷፯-፲፪

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- የእባብ ሥዕል በማዘጋጀት በምሥል የታገዘ ትምህርት ያስተምራቸው፡፡
- ልጆች እባብ አይታችሁ ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች አዳም ከሔዋን ጋር በውቧ ገነት ይኖር እንደነበረ፤ እግዚአብሔርም "መልካምና ክፉውን ከሚያስታውቀው የዕፀ በለስ ዛፍ አትብላ" ብሎት እንደነበር ታስታውሳላችሁ? ሰይጣን እግዚአብሔርን እና አዳምን ለማጣላት በእባብ ላይ አድሮ ለሔዋን ክፉ ምክር አቀረበ፡፡ ተንኮለኛው እባብ ሔዋንን "በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዟልን?›› አላት፡፡ ሴቲቱም ለእባቡ "በገነት ካለው ከዛፉ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን ዕፀ በለስን እንዳንበላ እግዚአብሔር አዞናል" አለችው፡፡ ተንኮለኛው እባብም "ሞትን አትሞቱም ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ ይከፈታሉ እንደ እግዚአብሔርም መልካምና ክፉውን ታውቃላችሁ" አላት፡፡ ፈታኙ እባብ ያቀረበውን ክፉ ምክር ሴቲቱ ሰማችው፤ ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ፤ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፤ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች፡፡ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለአዳምም ሰጠችው እርሱም ከእርሷ ጋር በላ፡፡ አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ሕግ ተላለፉ፡፡ እግዚአብሔርም በቃሉ ስላልታመኑለት አዘነ፡፡ እግዚአብሔርም ወደ ገነት መጣ፤ አዳምም በገነት ጫካዎች ተደበቀ፡፡ እግዚአብሔር "አዳም! አዳም! አዳም! ወዴት ነህ?" አለው፡፡ አዳምም "በገነት ድምፅህን ሰማሁ ራቁቴን ስለሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸሸግሁም" አለው፡፡ እግዚአብሔርም አዳምና ሔዋንን ቀጣቸው፡፡ ከውቧ ገነትም አባረራቸው፤ ገነትንም የሚጠብቅ የምትገለባበጥ የእሳት ሰይፍ የያዘ መልአክ አስቀመጠ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ልጆች እግዚአብሔር የማይሰሙትንና የማይታመኑትን ሰዎች ይቀጣል፡፡ ለአዳምና ለሔዋን የፍቅር ሕግ ሰጠ፤ ባለመታመናቸው ቀጣቸው ተንኮለኛውን እባብንም ረገመው፡፡ እግዚአብሔር የሚሰሙትን እና ትእዛዙን የሚጠብቁትን ልጆች በጥበብና በሞገስ ያሳድጋል፡፡

## *ጥያቄዎች*

1.ልጆች አዳምና ሔዋንን ማን ፈተናቸው?

2.እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን አትብሉ ያላቸው ዛፍ ምንድን ነው?

3.እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ለምን ከገነት አባረራቸው?

## ተግባር

- መምህሩ አንድ ሕፃን ታሪኩን በአጭሩ እንደገና እንዲተርክ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ኖህ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ኖህ ለእግዚአብሔር የነበረውን ፍቅርና ታማኝነት፤ እግዚአብሔርም ለኖህ የነበረውን ፍቅርና ያደረገውን ጥበቃ ማሳየት

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ ወደ መርከብ ግባ" ዘፍ.፯÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፯÷፯፣ ዕብ. ፲፩÷፯ እና ፪ጴጥ. ፪÷፯

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- በቅርጻ ቅርጽ የተሠራ መርከብና የተለያዩ እንስሳትን ለኖሙና በማቅረብ የጥፋት ውኃው የሚፈጥረውን ክሥተት እንዲያብራሩ ይጠይቃቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ኖህ የላሜህ ልጅ ነው፡፡ እንደ አያቱ እንደ ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፡፡ በእርሱ ዘመን የኖሩ ሰዎች ክፉዎች ነበሩ፤ እርሱ ግን መልካም ሰው ነበር፡፡ የዘመኑ ሰዎች ዓመጻን ያበዙ፤ በደልን እንደ ልብስ የተጎናፀፉ ሥርዓተ አልበኞች ነበሩ፡፡ ኖህ ግን ጻድቅ ነፍሱን ለእግዚአብሔር አስገዝቶ የኖረ የጽድቅ ሰባኪ ነው፡፡ ኖህ ከክፉው የዓለም ሥርዓት በመለየት እግዚአብሔርን በሚያስደስት ሕይወት ይኖር ነበር፡፡

እግዚአብሔር በኖህ ዘመን በኖሩ ሰዎች አዘነ፤ የንስሐም ጊዜ ሰጣቸው፡፡ ነገር ግን ሊመለሱ ፈቃደኞች ስላልሆኑ ሊቀጣቸው ፈረደ፡፡ ከዕለታት በአንድ ቀን እግዚአብሔር ለኖህ የሕይወት መመሪያ ሰጠው፡፡ እንዲህም አለው፤ "የሥጋ ለባሽ ሁሉ ፍጻሜ በፊቴ ደርሶአል፤ ከእነርሱ የተነሣ ምድር በግፍ ተሞልታለች እኔ አጠፋቸዋለሁ፡፡ አንተ ግን የምትድንበትን መርከብ ከጎፈር እንጨት ሥራ" ኖህም መርከቡን እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሠራ፡፡

እግዚአብሔር ክፉዎችን የሚቀጣበት ጊዜ ደረሰ፡፡ ኖህንም "አንተና ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ ወደ መርከብ ግባ፤ ከንጹሕ እንስሳት ሁሉ ሰባት ሰባት ተባትዕና አንስት፤ ንጹሕ ካልሆኑ እንስሳት ሁለት ሁለት ተባዕትና አንስት፤ ከሰማይ ወፍም ሰባት ተባዕትና አንስት እያደረግህ በምድር ላይ ለዘር ይቀር ዘንድ ለአንተ ትወስዳለህ" አለው፡፡ ኖህም ቤተሰቦቹንና እንስሳትን ይዞ ገባ፤ እግዚአብሔርም መርከቡን ከኋላ ዘጋበት፡፡ የጥፋት ውኃ በምድር ላይ ሞላ፡፡ በቀጣዩ ሳምንት ትምህርታችን ኖህና ቤተሰቡ ወደ መርከቡ ከገቡና የጥፋት ውኃ በምድር ላይ ከሞላ በኋላ የሆነውን እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ኖህን ይወደው ነበር፡፡ ኖህም በትውልዱ ፍጹምና ጻድቅ ሰው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ክፉዎችን ሊቀጣ ሲል ኖህን መርከብ እንዲያዘጋጅ አዘዘው፡፡ ኖህም መርከብ ሠራ፡፡ ወደ መርከቡም እንዲገባ በታዘዘ ጊዜ ቤተሰቡንና እንስሳትን ይዞ ገባ፡፡

## ጥያቄዎች

1. የኖህ መርከብ ከምን እንጨት ተሠራ?
2. እግዚአብሔር ኖህን ለምን መርከብ ሥራ አለው?
3. እግዚአብሔር ኖህን ለምን ወደ መርከቡ ግባ አለው?

## ተግባር

- መምህሩ መርከብና በውስጧ የተለያዩ ተባዕትና እንስት እንስሳትን ሥለው በከለር እንዲቀቡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ኖህና መርከቡ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ኖህና ቤተሰቡን አድኖ ክፉዎቹን መቅጣቱን ማስረዳት፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ዝናቡም አርባ ቀንና ሌሊት በምድር ላይ ሆነ" ዘፍ.፯÷፲፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፯÷፰ እና ፩ጴጥ. ፫÷፳

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች መርከብ አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- መርከብ ለምን ይጠቅማል?
- ስለ መርከብ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ኖህና ቤተሰቡ የተለያዩ እንስሶችም ወደ መርከቡ እንደገቡ ታስታውሳላችሁ? የሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ፡፡ የጥፋት ውኃ በምድር ላይ ያለማቋረጥ ቀንና ሌሊት ዘነበ፡፡ ምድር በሚያጠፋ ውኃ ተጥለቀለቀች፡፡ ክፉ ሰዎች ወደ ኖህ መርከብ መግባት አልቻሉም፡፡ ቤቶቻቸው በጎርፍ ፈራረሱ፡፡ ምድር በውኃ ተሞላች፤ ተራሮች በውኃ ተሸፈኑ፣ ዓመፀኞቹም ሰጠሙ፤ ማንም ሸሽቶ ማምለጥ አልቻለም፡፡ የሕይወት እስትንፋስ ያለው ሁሉ ሞተ፡፡

ኖህና ቤተሰቡ ግን በመርከቡ ውስጥ ነበሩ፡፡ ውኃው በሞላ መጠን በመርከቡ ውኃውን እየቀዘፉ ወደ ተራሮች ከፍታ ወጡ፡፡ ሌሎች ሲሞቱ ኖህና ቤተሰቡ በመርከቡ ውስጥ ሆነው ከሞት ዳኑ፡፡ የጥፋት ውኃው በቆመ ጊዜ የኖህ መርከብ በአራራት ተራራ ዐረፈች፡፡ ኖህም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ፡፡ እግዚአብሔርም በሕያው ነፍስ መካከል ዳግመኛ በጥፋት ውኃ ምድርን ላያጠፋ ቃል ኪዳን አደረገ፤ የስምምነቱም ምልክት ቀስተ ደመና ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ክፉዎችን በጥፋት ውኃ አጠፋ፤ ኖህና ቤተሰቡን የተመረጡ እንስሳትንም ከሞት አዳነ፡፡ እግዚአብሔርን የሚታዘዙ ከሞት ይድናሉ፡፡

www.zeorthodox.org

## *ጥያቄዎች*

1. እግዚአብሔር ኖህን ለምን አዳነው?
2. የጥፋት ውኃው በምድር ላይ ምን ያህል ጊዜ ቆየ?
3. የጥፋት ውኃው ሲቆም የኖህ መርከብ ማን በሚባል ተራራ ዐረፈች?
4. እግዚአብሔር ከኖህ ጋር ላደረገው ቃል ኪዳን ምልክቱ ምንድን ነው?

## ተግባር

መምህሩ በቃል የሚጠናውን ጥቅስ እንዲያስታውሱ ይጠይቃቸው?

www.zeorthodox.org

# እንዴት እንጸልይ?

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ሕፃናት እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ማሳወቅ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ሳታቋርጡ ጸልዩ በሁሉ አመስግኑ” ፩ተሰ. ፭÷፲፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፮÷፭-፲፫ እና ፊልጵ. ፬÷፮

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ጸሎት ምንድን ነው?
- ልጆች በቀን ስንት ጊዜ ይጸለያል?
- የጸሎትን አስፈላጊነት ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ጸሎት ከአባታችን ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበት መሣሪያ ነው፡፡ ጸሎት ለሕፃናት በጣም ያስፈልጋል፤ ስለዚህ በየዕለቱ መጸለይ አለብን፡፡ ስንጸልይ ማድረግ ያለብን፡-

በመጀመሪያ እንቆማለን፡፡ ከዚያ በትምህርተ መስቀል እናማትባለን፡፡ “በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ” እንላለን፡፡

በእግዚአብሔር ፊት እንደቆምን ማሰብ አለብን፡፡ ወደጎን መዞር፤ ሰው መመልከት የለብንም፡፡ ዓይኖቻችንን ወደ ሰማይ እናነሣለን፤ በሰማያት ከፍታ ያለውን እግዚአብሔርን በጸሎት መንፈስ ማነጋገር እንጀምራለን፡፡

### *ምግብ ስንመገብ*

“አባቴ እግዚአብሔር ሆይ የወላጆቼን ድካም ለፍሬ አብቅተህ ይህንን ማዕድ በፊቴ ስለዘረጋህ አመሰግንሀለሁ፡፡ ወላጆቼን ጠብቅ እንዳግዛቸው እኔን በጽድቅ አሳድገኝ፡፡ ብለን አባታችን ሆይና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሚሉ ጸሎቶችን ጸልየን አማትበንና ባርከን እንመገባለን፡፡

www.zeorthodox.org

### *ማታ ስንተኛ ደግሞ*

“አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ በሰላም ስላዋልከኝ ተመስገን፡፡ በሰላም አሳድረኝ” በማለት አቡነ ዘበሰማያትና በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል እንጸልያለን፡፡

### *ጠዋት ስንነሣ*

“ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ሆይ በሰላም ስላሳደርከኝ ስምህ ይመስገን በሰላም አውለኝ” በማለት አቡነ ዘበሰማያትና በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል እንጸልያለን፡፡

ልጆችን እግዚአብሔር ይወዳቸዋል፣ ይሰማቸዋል፣ አይንቃቸውም፡፡ ስለዚህ የምትፈልጉትን ጠይቁት የሚያስፈልጋችሁን ያደርግላችኋል፡፡

ጸሎታችንን ስንጨርስ “አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር፤ ስምህ ይቀደስ” በማለት ጌታ እንዳስተማረን እና ‹‹ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ  በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ. . . ››  በማለት ቅዱስ ገብርኤልም እንዳስተማረን እንጸልያለን፡፡

## ማጠቃለያ

ጸሎት ከአባታችን ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበት መሣሪያ ነው፡፡ የሚጸልዩ ልጆችን እግዚአብሔር ያሳድጋቸዋል ይባርካቸዋል፡፡ ስለዚህ በየዕለቱ ሳናቋርጥ መጸለይ ይገባናል፡፡

### *ጥያቄዎች*

፩. ማታ ስንተኛ ምን ብለን እንጸልያለን?

፪. በትምህርተ መስቀል ለምን እናማትባለን?

፫. በጸሎታችን ሁሉ መጨረሻ የምንጸልየው ጸሎት ምንድን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ “አቡነ ዘበሰማያትን” ያስጠናቸው፡፡
- የማማተብን ትርጉም ያስታውሳቸው፡፡
- አንዱን ሕፃን አስነሥቶ በተግባር እንዴት እንደሚጸልይ ለጓደኞቹ  እንዲያሳይ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ዳዊትና ዮናታን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች መልካም ነገሮችን ከባልንጀሮቻቸው ጋር እንዲካፈሉ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ዮናታን የለበሰውን ካባ አውልቆ ልብሱንም ለዳዊት ሸለመው” ፩ሳሙ. ፲፰÷፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ሳሙ. ፲፯÷፵፬ ፤ ፲፰÷፫ እና ሮሜ. ፲፪÷፱-፲፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ልጆች ከባልንጀሮቻቸው ምን ሊካፈሉ እንደሚችሉ ይጠይቃቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ዳዊት በቤተልሔም ይሁዳ እሴይ ከተባለ ሰው ተወለደ፡፡ በአባቱ ቤት የሁሉም ታናሽ ሲሆን የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር፡፡ ከዕለታት በአንድ ቀን ፍልስጥኤማውያን እስራኤላውያንን ጦራቸውን አዝምተው ወረሩ፡፡ በፍልስጥኤማውያን ሠራዊት ውስጥ ጎልያድ የሚባል እጅግ ግዙፍ የሆነ ወታደር ነበር፡፡ የእስራኤል ሠራዊት ግዙፉን ጎልያድን ፈሩት፤ ጎልያድም የእስራኤልን ሠራዊት አስፈራራ፡፡ ዳዊት የእስራኤልን ሠራዊት ያስፈራውን ግዙፉን ጎልያድን በወንጭፍ ድንጋይ ጣለ፤ ገደለውም፡፡ የትግሉም አሸናፊ በመሆኑ የብዙዎች መደነቂያ ሆነ፡፡

ዮናታን ደግሞ የእስራኤል ንጉሥ የሳኦል ታላቅ ልጅ ነው፡፡ ሕዝብ ያከብረው የነበረ ጀግና የጦር አለቃም ነበር፡፡ ከዳዊት ጋር ተግባቡ፤ ቃልኪዳን አደረጉ፤ የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች፤ ልባዊ በሆነ የወንድማማችነት ፍቅር ተዋድደው አብረውም ይጫወቱ ነበር፡፡

ዮናታንም የለበሰውን ካባ አውልቆ ልብሱንም ሰይፉንም ቀስቱንም መታጠቂያውንም ለዳዊት ሸለመው፡፡ በዳዊት የመከራ ቀን ሁሉ ዮናታን አብሮት ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች እንደ ዮናታንና እንደ ዳዊት መልካም ነገሮችን ሊካፈሉ፤ በፍቅር ሆነው በጋራ ሊጫወቱ፤ ሊመገቡ፤ ወደ ቤተክርስቲያን ሊመጡና ሊጸልዩ ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

## ጥያቄዎች

፩. በዛሬው ትምህርት ያነሣናቸው ባለ ታሪኮች እነማን ነበሩ?

፪. ካባውን አውልቆ የሸለመው ማን ነው?

፫. ልጆች ምን ምን ሊካፈሉ ይገባል?

## ተግባር

ሩ ልጆች በጋራ እንዲጫወቱ ያላቸውንም በጋራ እንዲጠቀሙ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ጠፈቤን በዓሣ ሞላ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃያልነት፤ ሁሉን ቻይነትና ተአምር አድራጊነት ለልጆች በማስተማር ልጆች በአቅማቸው ሌሎችን ማገልገል እንዲችሉ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል" ሉቃ. ፲፰÷፳፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ. ፭÷፩-፲፩፣ ማር. ፯÷፶፯ እና ዮሐ. ፳፩÷፬-፰

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ዓሣ አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- ዓሣዎች እንዴት በባሕር ይኖራሉ?
- ዓሣን እንዴት ማጥመድ ይቻላል?
- ከደቀመዛሙርቱ መካከል ዓሣ አጥማጆች የነበሩት እነማን ናቸው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጴጥሮስና ጓደኞቹ ዓሣ ያጠምዱ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ሌሊቱን ሙሉ ዓሣ መያዝ አልቻሉም፡፡ ደክመው ተስፋ ቆርጠው ሊመለሱ ሲሉ በጌንሴሬጥ ባሕር ዳር ኢየሱስ ቆሞ ነበር፡፡ በጴጥሮስም ጀልባ (ታንኳ) ሆኖ ሕዝቡን ያስተምር ነበር፡፡ ጌታ ትምህርቱን እንደጨረሰ ስምዖን ጴጥሮስን "ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል! መረቦቻችሁን ለማጥመድ ጣሉ" አለው፡፡ ጴጥሮስም "ጌታ ሆይ ሌሊቱን ሁሉ ስንደክም አደርን፤ ምንም አልያዝንም፤ ነገር ግን በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ" ብሎ ታዘዘው፡፡

የኢየሱስንም ትእዛዝ ተቀብለው ይህን ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፡፡ ከዓሣውም ብዛት የተነሣ መረቦቻቸው ተቀደዱ፡፡ በሌላ ታንኳ የነበሩትን ጓደኞቻቸውን እንዲያግዟቸው ጠሩ፡፡ ከጓደኞቻቸው ጋር ተጋግዘው በሁለቱ ታንኳዎች ዓሣ ሞሉ፡፡

ስምዖን ጴጥሮስም መረቡን በዓሣ የሞላውን ጌታችን ኢየሱስን "ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ" አለው፡፡ ጌታም "አትፍራ ከእንግዲህ ሰው የምታጠምድ ትሆናለህ" አለው፡፡ መረባቸውን በዓሣ ስለሞሉ ዮሐንስ፣ ያዕቆብና በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ተደነቁ፡፡ ታንኳዎቻቸውንም ወደ ምድር አድርሰው ሁሉን ትተው ተከተሉት፡፡ ደቀመዛሙርቱም ሆኑ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ተአምራትን አድርጓል፡፡ ተአምራቱ ሁሉ ሕዝቡን ያስደስቱ ያስደንቁም ነበር፡፡ ደቀመዛሙርቱም ይህን አይተው፤ ሁሉን ትተው ተከተሉት፡፡ እርሱ በእርግጥ የጎደለውን ጓዳ ሞልቶ በበረከት ያትረፈርፋል፡፡

## ጥያቄዎች

1. ጌታችን ኢየሱስ በጌንሴሬጥ ባሕር ዳር በማን ጀልባ (ታንኳ) ላይ ተቀምጦ አስተማረ?
2. ከስምዖን ጴጥሮስ ጋር ዓሣ ያጠምዱ የነበሩ ሁለቱ የዘብዴዎስ ልጆች እነማን ነበሩ?
3. ስምዖን ጴጥሮስ ታንኳዎቹ በዓሣ ሞልተው ሲያይ ጌታን ምን አለው?

## ተግባር

- ሕፃናት ምግብ ከመመገባቸው በፊት እንዲጸልዩ ይምከራቸው፡፡
- ከልጆቹ መካከል አንዱ ታሪኩን ደግሞ እንዲተርክ ይጋብዝ፡፡
- ልጆች በሚችሉት ሁሉ ቤተሰቦቻቸውን እንዲያገለግሉ ያበረታታቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ኢየሱስ በቤተ ሳይዳ የሚኖረውን ሕመምተኛ /በሽተኛ/ ፈወሰ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ኢየሱስ ክርስቶስ ፈዋሽ መድኃኒታችን እንደሆነ ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ” ዮሐ. ፭÷፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፭÷፩-፲፭

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች አሟችሁ ያውቃል?
- የታመመ ሰው አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- በሽታ ምንድን ነው?
- ልጆች ስንታመም ምን ማድረግ አለብን?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በኢየሩሳሌም በበጎች በር አጠገብ አንዲት መጠመቂያ ነበረች፡፡ በዕብራይስጥ ቤተሳይዳ ትባላለች፡፡ አምስት መመላለሻዎች ነበሩባት፡፡ በእነዚህ ውስጥ የውኃውን መንቀሳቀስ እየጠበቁ በሽተኞች፣ ዕውሮች፣ አንካሶችም፣ ሰውነታቸውም የሰለለ ብዙ ሕሙማን በመጠመቂያው ውኃ ውስጥ እየገቡ ይተኙ ነበር፡፡

አንዳንድ ጊዜ የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያ ወርዶ ውኃውን ያናውጥ ነበር፡፡ ከውኃው መናወጥ በኋላ በመጀመሪያ የገባ ከማናቸውም ካለበት ደዌ ሁሉ ተፈውሶ ጤናማ ይሆን ነበር፡፡ በዚያም ለሠላሳ ስምንት ዓመት የታመመ አንድ ሰው ነበር፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤተ ሳይዳ በመጣ ጊዜ ይህን ብቸኛ ረዳት የሌለው ሕመምተኛ አየው፡፡ ብዙ ዘመንም እንዲሁ እንደነበር ስላወቀ “ልትድን ትወዳለህን?” ብሎ ጠየቀው፡፡

ድውዩም “ጌታ ሆይ ውኃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም፤ ነገር ግን እኔ ስመጣ ሳለሁ ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል” ብሎ መለሰለት፡፡

ጌታችን ኢየሱስም “ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ” ብሎ አዘዘው፡፡ ወዲያው ሰውዬው ዳነ አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ፡፡ በጣም ደስተኛ ሆነ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ተአምራትን አድርጓል፡፡ ሁሉን ቻይ አምላክ ስለሆነ የሚሳነው የለም፡፡ ጠያቂ፣ ደጋፊ ሰው የሌላቸውን ይጎበኛል፡፡ ሕሙማንን ይፈውሳል፡፡ ሙታንን ያስነሣል፡፡

## ጥያቄዎች

1. የመጠመቂያይቱ ስም በዕብራይስጥ ማን ትባል ነበር?
2. መጠመቂያይቱ ስንቱ መመላለሻዎች ነበሩአት?
3. በደዌ የተያዘው ሕመምተኛ ምን ያህል ጊዜ በሕመም ቆየ?

## ተግባር

- መምህሩ ከልጆቹ መካከል አንዱን ታሪኩን እንዲተርክ ይጋብዝ፡፡
- ሕፃናት ለሕሙማን እንዲጸልዩ ያበረታታቸው፡፡
- ልጆች "መዝሙር ፳፪"ን በጋራ እንዲያነቡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሶምሶንና አንበሳው

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ከእኛ ጋር እንደሆነና አብሮነቱ ከክፉ ነገር ሁሉ እንደሚ ያድነን ማሳወቅ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?" መዝ. ፳፯÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መሳ. ፲፫÷፲፬ እና ሮሜ ፰÷፳፰

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- መምህሩ ሕፃናት ምን እንደሚፈሩ ይጠይቃቸው፡፡
- ልጆች አንበሳ ታውቃላችሁ?
- ልጆች አንበሳ ትፈራላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሶምሶን የሚባል አንድ ወጣት ነበር፡፡ አባቱ የዳን ነገድ የሆነ ማኑሄ የሚባል ሰው ነበር፡፡ እናቱ መካን ነበረች፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ ልጅ እንደምትወልድ ነገራት፡፡ ሶምሶን ከልደቱ ጀምሮ ናዝራዊ ስለነበረ ፀጉሩን አይላጭም፤ የሚያሰክር መጠጥም አይጠጣም ነበር፡፡ የእግዚአብሔርም ኃይል በፀጉሩ ነበረ፡፡

በአንድ ወቅት ሶምሶን ከእናቱና ከአባቱ ጋር ወደ ተምና ከተማ ሄደ፡፡ ሶምሶን በተምና ከተማ ወዳለው የወይን ስፍራ መጣ፡፡ አንድ የአንበሳ ደቦል እያገሳ ወደ እርሱ መጣበት፡፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል ወረደ፡፡ ሶምሶን ጠቦትን እንደሚቆራርጥ ያለ መሣሪያ አንበሳውን ቆራረጠው፡፡

ከጥቂት ቀን በኋላ የአንበሳውን ሬሳ ሊያይ ተመለሰ፡፡ እነሆም በአንበሳው ሬሳ ውስጥ ንብ ሰፍሮበት ነበር፤ ማርም ነበረበት፡፡ በአንበሳው መንጋጋ የተከማቸውን ማር ወስዶ መንገድ ለመንገድ እየበላ ሄደ፡፡ ማሩንም ለአባትና ለእናቱ ሰጣቸው እነርሱም በሉ፡፡ ከአንበሳው ሬሳ ማሩን እንደወሰደ ግን አልነገራቸውም ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ሶምሶን ጠንካራ ወጣት ነበር፤ የእግዚአብሔርም ኃይል በእርሱ ነበር፡፡

ሶምሶን አንበሳ ገደለ፡፡ ከአንበሳውም አፍ ያገኘውን ማር ከወላጆቹ ጋር ተካፍሎ በላ፡፡ እግዚአብሔር ከክፉ ነገር መልካም ማውጣት እንደሚችል፤ ዘወትርም ሳያንቀላፉ ከክፉዎች እንደሚጠብቀን የሶምሶን ታሪክ ያስተምረናል፡፡

### ጥያቄዎች

፩. ልጆች ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

፪. የሶምሶን አባት ማን ነበር?

፫. የእግዚአብሔር ኃይል በሶምሶን በየትኛው የአካል ክፍሉ ነበር?

## ተግባር

- መምህሩ ከሕፃናት መካከል አንዱ ታሪኩን ደግሞ እንዲተርክ ይጋብዝ፡፡
- የአንበሳ ሥዕል በማዘጋጀት ስለ አንበሳ ኃያልነት ይንገራቸውና ሶምሶን እንዴት ሊያሸንፍ እንደቻለ ያስረዳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሶምሶን ኃይሉን አጣ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ሁላችንንም እንደባረከንና ከጸጋ ጋር እንደፈጠረን በማስተማር ጸጋውን በአግባቡ ካልያዝን እንደሚወስድብን ማስረዳት

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፡፡" መዝ. ፳፮÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መሳ. ፲፮ እና ፩ቆሮ ፲፪÷፬-፳፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ሶምሶን ለምን ጠንካራና ኃያል ሰው እንደሆነ ይጠይቃቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሶምሶን የእስራኤል የመጨረሻ መስፍን ነበረ፡፡ ሶምሶን ፍልስጥኤምን እንዲወጋ ኃይል ከእግዚአ ብሔር ተቀበለ፡፡ አንዲት ፍልስጥኤማዊት ሚስት አገባ፡፡ በእርሷም ምክንያት በተጣሉ ጊዜ እህላቸውን አቃጠለ፡፡ በአንድ የአህያ መንጋጋ አንድ ሺህ ፍልስጤማውያንን ገደለ፡፡

በአንድ ወቅት ጠላቶቹ በጋዛ ከተማ ሊይዙት ሲጠባበቁት የከተማይቱን በር መዝጊያ ነቅሎ በመውሰድ አመለጠ፡፡

ሶምሶን ደሊላ የምትባል ሴት ወደደ፡፡ ይህች ሴት ኃይሉ ያለበትን የአካል ክፍል፤ የናዝራዊነቱን ምስጢር እስኪነግራት ድረስ በፍቅር አታለለችው፡፡ ኃይሉ በፀጉሩ እንደሆነ ሲነግራት ፀጉሩን ላጭታ ሲደክም ለፍልስጥኤማውያን መኳንንት አሳልፋ ሰጠችው፡፡ ሶምሶን ኃይለኛ የሆነው በእምነት ነበር፡፡ ራሱን ባለመግዛቱ ምክንያት ኃይሉን አጣ፡፡ ጠላቶቹ በእስር ቤት ጣሉት፡፡ ዓይኖቹን አውጥተው አሳወሩት፡፡

## ማጠቃለያ

የእግዚአብሔርን ስጦታ በእምነት ተቀብለናል፤ ራስን በመግዛትና በጸሎት ጸጋውን ልንጠብቅ ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

## ጥያቄዎች

1. ሶምሶን ለምን ኃይሉን አጣ?
2. ሶምሶንን ያታለለችው ሴት ማን ናት?
3. የእግዚአብሔርን ስጦታዎች እንዴት እንጠብቃለን?

## ተግባር

- መምህሩ የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታዎች እንዲዘረዝሩ ይጠይቃቸው፡፡
- በቃል የሚጠናውን መነሻ ጥቅስ እንዲያስታውሱ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ገብርኤል እና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ቤተክርስቲያን ለልደት በዓል በምታደርገው ዝግጅት መተባበርና ከደስታዋም መካፈል እንዳለብን ማስተማር

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከሴቶች መካከል አንቺ የተባረክሽ ነሽ" ሉቃ. ፩÷፳፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ. ፩÷፳፮-፶፮

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የመላእክት አገልግሎት ምንድን ነው?
- ልጆች መላእክትን ወደ እኛ የሚልካቸው ማነው?
- ልጆች የምታውቁትን የመላእክት ስም ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱስ ገብርኤል በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም ሊቀ መላእክት ነው፡፡ ድንግል ማርያም ደግሞ ከኢያቄምና ከሐና በሕጋዊ ጋብቻ የተወለደች፤ በቤተመቅደስ ያደገች፤ ለእግዚአብሔር ወልድ ማደሪያነት የተመረጠች ምድራዊት እርያም ናት፡፡

ከዕለታት በአንድ ቀን ቅዱስ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ መጣ፤ ድንግል ማርያምም ደጉን መልአክ ገብርኤልን አየች፡፡ መልአኩ ገብርኤል "ደስ ይበልሽ፤ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ካንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ" አላት፡፡

ድንግልም በሰላምታው ቃል ተደንቃ "ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?" አለች፡፡ መልአኩም "ማርያም ሆይ አትፍሪ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን አግኝተሻል፤ እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፤ እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፡፡ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፡፡ በያዕቆብ ቤትም ለዘላለም ይነግሣል፤ መንግሥቱም መጨረሻ የለውም" አላት፡፡

ድንግል ማርያምም "ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?" አለችው፡፡ መልአኩ ገብርኤልም "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ ዘመድሽ ኤልሳቤጥ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው፡፡ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም" አላት፡፡ ድንግል ማርያምም "እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" በማለት አመነች፡፡ አምላክንም በድንግልና ፀነሰች፡፡ ድንግል ደስ አላት አምላኳንም አመሰገነች፡፡



www.zeorthodox.org

ወዲያው ወደ አክስቷ ወደ ኤልሳቤጥ ቤት ሄደች፡፡ ሦስት ወራትም በዚያ ተቀመጠች፡፡

## ማጠቃለያ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ስለወለደች በጣም ደስተኛ ነበረች፡፡ ምክንያቱም እርሱ የዓለም ደስታ ስለሆነ ነው፡፡ ኢየሱስ አምላክ ነው፤ ድንግል ማርያምም የአምላክ እናት ናት፡፡

## *ጥያቄዎች*

፩. ድንግል ማርያምን ያበሰራት መልአክ ማን ነው?

፪. መልአኩ ገብርኤል ድንግልን በምን ዓይነት የሰላምታ ቃል ተናገራት?

፫. ድንግል ማርያም ማንን ወለደች?

## ተግባራት

- መምህሩ ልጆች የልደት በዓልን እንዴት እንደሚያከብሩ ያሳያቸው፡፡
- መምህሩ ልጆች የመልአኩን "የሰላምታ ቃል" በቃል እንዲይዙ ያስጠናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# እረኞችና መላእክት

**የትምህርቱ ዓላማ:-** ሰማያውያንና ምድራውያን በክርስቶስ ልደት ምክንያት በምስጋና እንደተባበሩ መግለጽ፤

**በቃል የሚጠና ጥቅስ:-** "እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃ. ፪÷፲

"ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ" ሉቃ ፪÷፲፬

**ተጨማሪ ምንባባት:-** ሉቃ. ፪÷፰-፳ እና መዝ. ፻፵፰÷፩-፫

www.zeorthodox.org

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች በጎች አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- ልጆች የእረኞች ሥራ ምንድን ነው?
- ልጆች የመላእክት፣ የበጎችና የእረኞች ሥዕል ሥላችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት:-

የኢየሩሳሌም እረኞች በየዕለቱ በጎችን በለምለም መስክ ያሰማራሉ፡፡ በጎቻቸውን ከአውሬ ለመጠበቅ በሌሊት በሜዳ ያድሩ ነበር፡፡ ከዕለታት በአንድ ቀን የጌታ መልአክ ወደእነርሱ ቀረበ፡፡ የእግዚአብሔርም ክብር በዙሪያቸው አበራ፡፡ ጨለማው በብርሃን ተተካ፡፡ እረኞቹ በሕይወታቸው አጋጣሚ አይተው የማያው ቁትን መልአክ ስላዩ ታላቅ ፍርሃት ፈሩ፡፡

መልአኩም "እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፡፡ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና ይህም ምልክት ይሆንላችኋል፡፡ ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግምም ተኝቶ ታገኛላችሁ፡፡" አላቸው፡፡

እረኞቹ በጣም ደስተኛ ሆኑ፡፡ ከተናገራቸው መልአክ ጋር ብዙ የሰማይ ሠራዊት ነበሩ፡፡ እረኞቹም ከሰማያውያኑ ሠራዊት ጋር "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ ይሁን" እያሉ ዘመሩ፡፡ መላእክቱ ወደ ሰማይ በተመለሱ ጊዜ እረኞቹ ወደ ቤተልሔም ገሰገሱ "እስከ ቤተልሔም እንሂድ እግዚአብሔር የገለጠልንን ይህን የሆነውን እንይ" እየተባባሉ ተጓዙ፡፡

ወደ ቤተልሔም በደረሱ ጊዜ ማርያምንና ዮሴፍን ሕፃኑን ኢየሱስን በግርግም ተኝቶ አገኙ፡፡ አይተውም ስለዚህ ሕፃን የተነገራቸውን ነገር ገለጡ፡፡ እረኞቹ እንደተባለላቸው ስለ ሰሙትና ስለ አዩት ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ ተመለሱ፡፡

## ማጠቃለያ

መላእክት ለእረኞቹ መልካም ዜና አመጡ፡፡ እረኞቹም የተነገረለትን ሕፃን ኢየሱስን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው፡፡ እኛም የጌታን ልደት በደስታ ልናከብር ይገባል፡፡

## ጥያቄዎች

፩. ልጆች መላእክትና እረኞች ምን እያሉ ዘመሩ?

፪. ኢየሱስ በየት ስፍራ ተወለደ?

፫. እረኞቹ ወደ ቤተልሔም በደረሱ ጊዜ ምን አዩ?

፬. የልደት በዓልን ለምን እናከብራለን?

## ተግባር

- መምህሩ ሕፃናት የመላእክትን ምስጋና እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡
- የልደት በዓል አከባበርን በጨዋታ መልክ እንዲለማመዱ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# አናጢው ቅዱስ ዮሴፍ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ቅዱስ ዮሴፍ ድንግል ማርያምን እንደጠበቃት፤ በጉዞዋ ሁሉ እንዳልተለያት ለልጆች ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ልጄን ከግብጽ ጠራሁት" ሆሴዕ. ፲፩÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፩÷፲፰-፳፭፤ ፪÷፲፫-፳ እና ሉቃ. ፪÷፩-፯፣ ፴፫÷ ፵፩-፶፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ድንግል ማርያምን እንዲጠብቅ ዮሴፍ እንዴት እንደተመረጠ ታውቃላችሁ?
- ልጆች ስለ አናጺው ዮሴፍ የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ዮሴፍ እንጨት በመጥረብ በአናጢነት ሥራ ይተዳደር የነበረ ሰው ነው፡፡ ከዳዊት ዘር የተወለደ ጻድቅ አረጋዊ ነበር፡፡ ድንግል ማርያምን እንዲጠብቅ ተመረጠ፡፡ በአንድ ወቅት አውግስጦስ ቄሳር ሕዝብ እንዲቆጠር ዓዋጅ አወጣ፡፡ ዮሴፍም ድንግል ማርያምን ይዞ ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ቤተልሔም ሄደ፡፡ በዚያም ሳሉ ድንግል ማርያም የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ፡፡ የበኩር ልጇን ወለደች፡፡ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በግርግምም አስተኛችው፡፡ በመልአኩ እንደተነገረው ስሙን ኢየሱስ አሉት፡፡

የጌታ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ "ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልጋልና ተነሣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ፤ ወደ ግብጽ ሸሽ እስከነግርህም በዚያ ተቀመጥ" አለው፡፡ ዮሴፍም ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ግብጽ ተሰደደ፡፡ በነቢይ "ልጄን ከግብጽ ጠራሁት" የተባለው ትንቢት ተፈጸመ፡፡ ሄሮድስ እስኪሞት በዚያ ተቀመጡ፡፡ ሄሮድስም ብዙ ሕፃናትን አስገደለ፤ ቤተልሔምንም በሕፃናት ደም አጥለቀለቃት፡፡

ሄሮድስም ከሞተ በኋላ የጌታ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ "የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል ሃገር ሂድ" አለው፡፡

ዮሴፍም ሕፃኑና እናቱን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፡፡ ከድንግል ማርያም አልተለየም፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን በቤቱ አሳደገ፡፡ ጌታ ዐሥራ ሁለት ዓመት ሲሆነው የፋሲካ በዓልን እንዲያከብር ወደ መቅደስ ይዞት ወጣ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ዮሴፍ ለቅዱሱ ቤተሰብ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በአናጢነት ሙያ ይተዳደር የነበረ ሰው ሲሆን ድንግልን ለመጠበቅ ተመርጧል፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ ብዙ ጊዜ ያናግረው ነበር፡፡ በመከራም ሆነ በደስታ ከድንግል ማርያምና ከልጇ አልተለየም ነበር፡፡

## *ጥያቄዎች*

፩. ዮሴፍ በምን ዓይነት ሥራ ይተዳደር ነበር?

፪. ዮሴፍ ወደ ቤተልሔም ከድንግል ማርያም ጋር የሄደው ለምን ነበር?

፫. ኢየሱስንና እናቱን ማርያምን ይዞ ወደ የት ሄደ?

፬. ዮሴፍ ወደ ግብጽ እንዲሄድ ወደ እስራኤልም እንዲመለስ ማን ነገረው?

፭. ኢየሱስን ሊገድል የፈለገው ማን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ የዮሴፍን ቤተሰብ ልጆች በሥዕል እንዲሣሉ ያድርግ፡፡
- የተማሩትን ይህን ታሪክ ለጓደኞቻቸው እንዲተርኩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ጦቢት እና መልአኩ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ቅዱሳን መላእክት በዙሪያችን እንዳሉ ለልጆች ማስገንዘብ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል" መዝ. ፺÷፲፩ እና ማቴ. ፬÷፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መፅሐፈ ጦቢት. ፩-፲፬ መዝ. ፺÷፩-፲፮

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች መላእክት በዙሪያችሁ እንደሚከቡ ታውቃላችሁ?
- ልጆች ማየት የተሳነው ሰው እንዴት ይራመዳል?
- ልጆች ስለ ጦቢት ልጅ ስለ ጦቢያ የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጦቢት እግዚአብሔርን የሚወድ መልካም ሰው ነበር፡፡ ጦቢት የተራቡትን የሚያበላ፣ የተጠሙትን የሚያጠጣ፣ የታረዙትን የሚያለብስና ለድሆች የሚቆረቆር ደግ ሰው ነበር፡፡ ከዕለታት በአንድ ቀን በቤቱ ወለል ተኝቶ ሳለ ወፎች ትኩስ ፋንዲያ በዓይኑ ላይ ጣሉበት፤ ዓይኑም ታወረ፡፡ ወደ ባለመድኃኒቶች ቢሄድም የፈወሰው የለም፡፡

ጦቢት ማየት ስለማይችል በቤት መዋል ጀመረ፤ ሥራም መሥራት አልቻለም፡፡ ስለዚህ ድሃ ሆነ፤ ቤተሰቡንም ማስተዳደር አልቻለም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔርን አላማረረም፡፡ "አቤቱ በሥራህ ሁሉ በፍርድህና በቸርነትህ እውነተኛ ነህ፡፡ ነፍሴን የሚቀበላት መልአክ እዘዝልኝ" አለ፡፡

ጦቢት ጦብያ የሚባል ልጅ ነበረውና አስጠርቶ "ልጄ በሞትኩ ጊዜ አክብረህ ቅበረኝ፤ እናትህንም ጠብቃት፤ በሕይወትም በኖርህበት ዘመን ሁሉ አክብራት፡፡ በዘመንህ ሁሉ ፈጣሪህን እግዚአብሔርን አስበው፤ ትእዛዙን መካድና በደልን አትውደድ፡፡ እውነትን ሥራ፡፡ በእውነት የኖሩ ሰዎች ሁሉ ሥራቸው ይከናወንላቸዋል፡፡ ከገንዘብህ ምጽዋት ስጥ፡፡ ለራስህ የጠላኸውን ለማንም አታድርግ፡፡ ከልብስህ ለተራቆተ ደሃ ስጥ፡፡ ከመምህራን ዘንድ ምክርን ፈልግ በየጊዜው እግዚአብሔርን አመስግነው፡፡" ብሎ መከረው፡፡

ጦቢት ለልጁ ለጦቢያ የሜዶን ክፍል በሚሆን ራጊስ በሚባል ቦታ በገባኤል ዘንድ አደራ ስላስጠበቀው ዐሥር ብር ነገረው፡፡ ሄደህም ዐሥሩን ብር አምጣ አለው፡፡

ጦቢያም "አባቴ ሆይ ያዘዝኸኝን ሁሉ እሠራለሁ" አለ፡፡ ወደ ሜዶንም ሊሄድ በተነሣ ጊዜ በመንገድ መልአኩ ሩፋኤልን



www.zeorthodox.org

አገኘው፡፡ መልአክ እንደሆነ ስላላወቀ “ወደ ሜዶን አብረኸኝ መሄድ ትችላለህ?” አለው፡፡

መልአኩ ሩፋኤልም “አዎ” አለው፡፡ ጦቢያም “መንገዱን ታውቀዋለህ?” አለው፡፡ መልአኩም “አዎ” አለ፡፡ ጦቢያም መልአኩን ወደ አባቱ አመጣው፡፡ ጦቢት መልአኩ ሩፋኤልን “ከማን ወገን ነህ? ከወዴት ሃገር መጣህ?” አለው፡፡

መልአኩም “የታላቅ ወንድምህ የአናንያ ዘመድ አዛርያ ነኝ” አለው፡፡ ጦቢት አብረው እንዲሄዱ ፈቀደላቸው፡፡ “ቸር መልአክ በፊታችሁ ይሂድ ጎዳናችሁን እግዚአብሔር ያቅናላችሁ በደኅና ይመልሳችሁ” ብሎ መርቆ ሸኛቸው፡፡ በመንገድም ሲሄዱ ውኃ ወደአለበት ደረሱ፡፡ ዓሣም አገኙ፡፡ መልአኩም “ዓሣውን እረደው” አለው፡፡ ጦብያም ዓሣውን አረደው፡፡ መልአኩ ሩፋኤል “ጉበቱን፣ ሃሞቱንና ልቡን አጥብቀህ ያዘው” አለው፡፡ ጦብያም መልአኩ እንዳዘዘው አደረገ፡፡

ወደ ሜዶን ሄዱ፡፡ ከገባኤል ያለውን ገንዘብ ይዘው ተመለሱ፡፡ ጦብያም የዓሣውን ሃሞት በአባቱ ዓይን ላይ ቀባው፡፡ “አባቴ እንድትድን እመን” አለው፡፡ ጦቢትም አመነ፤ ዳነም፤ ዓይኖቹ ተከፈቱ፤ ልጁን ጦብያን አየው፡፡ የጦቢያን አንገት አቅፎ ሳመው፡፡ ጦቢት በደስታ ብዛት አለቀሰ፡፡ ጦብያም በሜዶን የተደረገለትን ነገር ሁሉ ነገረው፡፡

ጦቢት ልጁን ጦብያን “ያ አብሮህ የተጓዘ ሰው ውለታ አለብንና ደሞዝ እንጨምርለት” አለው፡፡ መልአኩ ሩፋኤልንም ጠርተው ሲያናግሩት፤ “እግዚአብሔርን አመስግኑ ለርሱም ተገዙ ለስሙም ምስጋና አቅርቡ ክቡር ሥራውን በክብር ተናገሩ፡፡ እግዚአብሔር አንተን አድንህ ዘንድ ላከኝ፤ እኔ ከሰባቱ አለቆች አንዱ አለቃ መልአኩ ሩፋኤል ነኝ” አላቸው፡፡ ጦቢትና ጦቢያም እግዚአብሔርን አመሰገኑ መልአኩም ተልእኮውን ፈጽሞ ወደ ላከው ወደ እግዚአብሔር ተመለሰ፡፡

## ማጠቃለያ፡-

ልጆች እግዚአብሔር የሚያምኑትን በመላእክቱ ያስጠብቃል፡፡ ጦቢትና ቤተሰቡን እንዲረዳ መልአኩ ሩፋኤልን ላከላቸው፡፡ ቅዱስ ሩፋኤልም ከጦብያ ጋር እየተጓዘ ችግሮቻቸውን አስወግዶ ተመለሰ፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ከጦብያ ጋር ወደ ሜዶን የተጓዘው መልአክ ማን ነው?
2. እነ ጦቢያ ወደ ሜዶን የሄዱት ምን ሊሠሩ ነው?
3. መልአኩ ሩፋኤልን ወደ ጦቢያ የላከው ማን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ሕፃናት የመልአክ ሥዕል እንዲሠሩ ያድርግ፡፡
- መዝሙረ ዳዊት መዝሙር ዘጠናን እንዲያነቡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ነቢዩ ኤልሳዕና የመላእክት ጥበቃ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር መላእክቱን ልኮ ከመከራ እንደሚያድነን ለልጆች ማሳወቅ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “መልአኬ በፊትህ ይሄዳል፤ በመንገድህም ይጠብቅሃል፡፡” ዘፀ. ፳፫÷፳-፳፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፬ ነገ. ፮÷፰-፳፫ እና ዕብ. ፩÷፲፬

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች መልአኩ ሩፋኤል ጦብያን እንዴት እንደረዳው ታስታውሳላችሁ?
- ልጆች መላእክት ወደ እኛ ለምን እንደሚመጡ ታውቃላችሁ?
- ልጆች ስለ መላእክት አገልግሎት ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በአንድ የታሪክ ክሥተት ውስጥ ሁለት ነገሥታት ነበሩ፡፡ እነርሱም የእስራኤልና የሶርያ ነገሥታት ናቸው፡፡ የሶርያ ንጉሥ ከእስራኤል ጋር ሊዋጋ ፈለገ፡፡ እስራኤል ሠራዊት በሚያልፍበት ስፍራ ሠራዊቱ ድብቅ ምሽግ እንዲሠሩ አደረገ፡፡ ነገር ግን ነቢዩ ኤልሳዕ በመንፈስ ተረድቶ “ሶርያውያን በዚያ ተደብቀዋልና በዚያ ስፍራ እንዳታልፍ ተጠንቀቅ” ብሎ ለእስራኤል ንጉሥ መልእክት ላከ፡፡ የሶርያው ንጉሥ ምስጢሩ ስለታወቀበት እጅግ አዘነ፡፡ አገልጋዮቹን ጠርቶ “ከሠራዊታችን መሐል ከእስራኤል ንጉሥ ጋር ተወዳጅቶ ምስጢር የሚነግር አለን?” አላቸው፡፡ አገልጋዮቹም “እንዲህ አይደለም በእልፍኝህ ውስጥ የምትናገረውን በእስራኤል ዘንድ ያለ ነቢይ ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ይነግረዋል” አሉት፡፡ ንጉሡም “ሂዱና ግደሉት›› ብሎ ሠራዊቱን ላከ፤ በሌሊቱም መጥተው ከተማይቱን ከበቡ፡፡

የእግዚአብሔር ሰው የኤልሳዕ ሎሌ በማለዳ ተነሥቶ በወጣ ጊዜ በከተማይቱ ዙሪያ ጭፍራና ፈረሶች ሰረገሎችም ከበዋቸው ነበር፡፡ ወደ ኤልሳዕም ሮጦ “ጌታዬ ሆይ ወዮ ምን እናደርጋለን?” አለው፡፡ ኤልሳዕም “ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉና አትፍራ” አለው፡፡ ኤልሳዕም “አቤቱ ያይ ዘንድ ዓይኖቹን እባክህ ግለጥ” ብሎ ጸለየ፡፡ እግዚአብሔርም የብላቴናውን ዓይኖች ገለጠ፡፡ አየም፡፡

በኤልሳዕም ዙሪያ ያሉት የእሳት ፈረሶችና ሰረገሎች ተራራውን ሞልተውት ነበር፡፡ የኤልሳዕ ሎሌ ግያዝም አልፈራም፡፡ ኤልሳዕም የሠራዊቱን ዓይን አሳወረ፡፡ ምግብም መገባቸው፡፡ በመጡበትም መንገድ በሰላም መለሳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር መላእክቱን እየላከ ሕዝቡን ከመከራና ከጠላት ጦር ያድናል፡፡ መልካም ከሠራን መላእክቱ ከእኛ ጋር ይኖራሉ፤ ክፉ ከሠራን ግን ይለዩናል፡፡

## ጥያቄዎች

1. የኤልሳዕ ሎሌ ዓይኖቹን ሲገልጥ ምን ተመለከተ?
2. ሎሌው በፈራ ጊዜ ኤልሳዕ ምን አደረገ?
3. እግዚአብሔር መላእክቱን ወደ እኛ ለምን ይልካል?

## ተግባራት

- መምህሩ ከልጆች መካከል አንዱን ይህን ታሪክ ለጓደኞቹ እንዲነግር ይጋብዝ፡፡
- ልጆች የእግዚአብሔርን መላእክት ጠባቂነት የሚገልጥ መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ነቢዩ ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች በእግዚአብሔር በመታመን እንዲያድጉ መምከር

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር ዓሣውን አዘዘው፣ እርሱም ዮናስን በየብስ ላይ ተፋው" ዮናስ. ፪÷፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ትንቢተ ዮናስ ፩ እና ፪ ፣ ማቴ ፲፪÷፴፱

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ስለ ዮናስ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- ስለ ዮናስ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ዮናስ የሚባል አንድ ነቢይ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት እግዚአብሔር "ተነሥተህ ወደ ታላቂቱ ነነዌ ሂድ ከክፋታቸው እንዲመለሱ ስበክ" አለው፡፡ ዮናስ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ይኮበልል ዘንድ ተነሳ፡፡ ወደ ኢዮጴም ወረደ፡፡ ወደ ተርሴስ የምታልፍ መርከብ አገኘ፡፡ ከእግዚአብሔር ለመሸሽ ወደ ተርሴስ ይሄድ ዘንድ ዋጋ ሰጥቶ ወደ መርከቧ ገባ፡፡

እግዚአብሔር በባሕሩ ላይ ታላቅ ነፋስ አመጣ፡፡ ማዕበልም ተነሣ፡፡ መርከቢቱም ልትሰበር ቀረበች፡፡ መርከበኞቹም ፈሩ፡፡ እያንዳንዳቸውም ወደ አምላካቸው ጸለዩ፡፡ መርከቢቱ ከማዕበሉ አደጋ ድና ጉዞዋን እንድትቀጥል በውስጧ የነበረውን ዕቃ ወደ ባሕር ጣሉት፡፡ ዮናስ ግን በከባድ እንቅልፍ ተኝቶ ነበር፡፡

የመርከቡ አለቃ ወደ እርሱ ቀርቦ "ምነው ተኝተሃል? ተነሥተህ አምላክህን ጥራ" አለው፡፡ ዮናስም ከእንቅልፉ ተነሣ፡፡ መርከቢቱ በማዕበል እንደተናወጸች ተሳፋሪዎቹም እንደተጨነቁ አየ፡፡

መርከበኞቹ እርስ በርሳቸው "ይህ ክፉ ነገር በማን ምክንያት እንዳገኘን እናውቅ ዘንድ ኑ ዕጣ እንጣጣል" ተባባሉ፡፡ ዕጣም ተጣጣሉ፡፡ ልጆች ዕጣው በማን ላይ የሚወድቅ ይመስላችኋል?

ልጆች ዕጣው ከእግዚአብሔር ሊሰወር በሞከረው በዮናስ ላይ ወደቀ፡፡ ዮናስንም "ባሕሩ ጸጥ እንዲል ምን እናድርግ?" አሉት፡፡ ዮናስም "ይህ ታላቅ ማዕበል በእኔ ምክንያት እንዳገኛችሁ አውቃችኋልና እኔን ወደ ባሕሩ ጣሉኝ፤ ያን ጊዜ ባሕሩ ጸጥ ይልላችኋል" አላቸው፡፡

ሰዎቹ ግን እርሱን ለማዳን ወደ የብሱ ለመቅዘፍ ሞከሩ፡፡ ነገር ግን ባሕሩ አብዝቶ ይናወጥ ነበር፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔር እንዳያዝንባቸው ጸልየው ዮናስን ወደ ባሕሩ ጣሉት፡፡ ባሕሩም ከመናወጥ ጸጥ አለ፡፡ ሰዎቹ እግዚአብሔርን እጅግ ፈሩ



www.zeorthodox.org

ስዕለትም ተሳሉ፡፡

እግዚአብሔር ዮናስን የሚውጥ ታላቅ ዓሣ አንበሪ ላከ፡፡ ዮናስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ ቆየ፡፡ በዓሣ አንበሪው ሆድ ውስጥ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፡፡ እግዚአብሔርም የዮናስን ጸሎት ሰማ፡፡ ዓሣውንም አዘዘው፤ዓሣውም ዮናስን ወስዶ በየብስ ላይ ተፋው፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች እግዚአብሔር የሚያዘንን እያደረግን በታማኝነት ማደግ አለብን፡፡ የትም ብንሄድ ጉድጓድ ውስጥም ብንደበቅ እግዚአብሔር ያየናል፡፡ ከመንፈሱ ወዴትም መሄድ አይቻልም፡፡ ከፊቱም መሸሽ አይቻልም፡፡ ልጆች እግዚአብሔርን በመከራ ጊዜም ስንጠራው ጸሎታችንን ሰምቶ ያድነናል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ልጆች ዮናስ ዋጋ ከፍሎ ወደ መርከብ የገባው ወዴት ለመሄድ ነበር?
2. ዮናስ ወደ መርከቧ ከገባ በኋላ እግዚአብሔር ምን አደረገ?
3. ዮናስ በዓሣ አንበሪው ሆድ ውስጥ ምን ያህል ቀናት ቆየ?
4. እግዚአብሔር ዮናስን የቀጣው ለምንድን ነው?
5. ከዮናስና ከዓሣው ማንኛው ለእግዚአብሔር ታዘዘ?
6. የብስ ምንድን ነው?

## ተግባራት

- መምህሩ ልጆቹ በዓሣ ሆድ ውስጥ ያለ ሰውን የሚያሳይ ሥዕል እንዲሥሩ ያድርግ፡፡
- ታሪኩን በአጭሩ እንዲከልሱ ይጠይቃቸው፡፡
- እግዚአብሔርን በመታዘዝ ስለሚገኘው በረከት ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ነቢዩ ዮናስ እና ቅሉ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእግዚአብሔርን ምሕረትና ርኅራኄ ለልጆች በማሳወቅ ለሌሎች መልካም እንዲያስቡ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አንተ ቸርና ይቅር ባይ ታጋሽም ምሕረትህ የበዛ አምላክ እንደሆንክ አውቄ ነበር" ዮናስ. ፬÷፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮናስ ፫ እና ፬

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ከዮናስ ታሪክ ምን ተማራችሁ?
- ሰው ከእግዚአብሔር ዓይን መሰወር ይችላል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ዮናስ ከዓሣ አንባሪው ሆድ ከወጣ በኋላ ወደ ታላቂቱ ነነዌ ሄደ፡፡ "ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ ንስሐ ግቡ በሦስት ቀን ነነዌ ትገለበጣለች" እያለ በከተማዋ ሰበከ፡፡ የነነዌ ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ፡፡ ለጾም ዓዋጅ ነገሩ፡፡ ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ ማቅ ለበሱ፡፡ ሦስት ቀን ጾሙ ጸለዩ፡፡

እግዚአብሔር በሕዝቡ መመለስ ተደሰተ፡፡ ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ፡፡ ሊያደርግባቸው የነበረውን ክፉ ነገርም ተወ፡፡ ቁጣውን በምሕረት መለሰ፡፡

ዮናስ ግን ተቆጣ፡፡ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይቅርታ ማድረጉ አላስደሰተውም፡፡ ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ፡፡ "በአገሬ ሳለሁ የተናገርሁት ይህን አልነበረምን? አንተ ቸርና ይቅር ባይ ታጋሽም ምሕረትህም የበዛ አምላክ እንደሆንክ አውቄ ነበርና፡፡ ስለዚህ ወደ ተርሴስ ለመኰብለል ፈጥኜ ነበር፡፡ አሁንም ከሕይወት ሞት ይሻለኛል፡፡ አቤቱ እባክህ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ" አለ፡፡

ዮናስም ደክሞት ተቀመጠ፡፡ እግዚአብሔርም ቅል አዘጋጀ፡፡ ቅሊቱም ለዮናስ ጥላ እንድትሆን ከፍ ከፍ አደረጋት፡፡ ዮናስም ስለ ቅሊቱ እጅግ ደስ አለው፡፡ በነጋው ቅሊቱን ትል በላት፤ ደረቀችም፡፡ ዮናስን እስኪዝል ድረስ ፀሐይ ራሱን መታው፡፡ ዮናስም ተቆጣ፡፡ እግዚአብሔር ዮናስን "አንተ ትበቅል ዘንድ ላልደከምክባት ላላሳደግሃትም በአንድ ሌሊት ለበቀለች ቅል ካዘንክ እኔስ ቀኛቸውንና ግራቸውን ለማያውቁ ከመቶ ሃያ ሺሕ ለሚበልጡ ሰዎችና ብዙ እንስሳት አላዝንምን?" አለው፡፡

www.zeorthodox.org

# ማጠቃለያ

ልጆች እግዚአብሔር የማንንም ሞት አይፈልግም፡፡ እግዚአብሔር መሐሪና ታጋሽ ቸርና ይቅር ባይ ነው፡፡ ልጆች በምሕረቱና በይቅርታው ደስ ይበላችሁ፡፡ እናንተም ክፉን በክፉ አትቃወሙ፡፡ በየቀኑ ለጓኞቻችሁ መልካም አድርጉ፡፡

## ጥያቄዎች

1. የነነዌ ሰዎች ስንት ቀን ጾሙ?
2. ልጆች እግዚአብሔር የነነዌ ሰዎችን በመማሩ ዮናስ ለምን አዘነ?
3. እግዚአብሔር ዮናስን እንዴት አስተማረው?

# ተግባር

- መምህሩ ልጆቹ ከዮናስ ታሪክ ምን እንደተማሩ ይጠይቃቸው፡፡
- በቃል የሚጠናውን ጥቅስ በጋራ እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሕፃኑ ሳሙኤል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በእግዚአብሔር መቅደስ መልካም ማድረግና መጸለይ እንደሚገባ ለልጆች ማስተማር

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አቤቱ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር" ፩ሳሙ. ፫÷፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ሳሙ ፩÷፩-፳፰፤ ፪ እና ፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ስለ ሳሙኤል እናት ስለ ሐና የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ልጆች በቤተክርስቲያን መደረግ ስላለበት ነገር ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሐና የምትባል አንዲት ሴት ነበረች፡፡ በተራራማው በኤፍሬም ሃገር ይኖር ከነበረው ከሕልቃና ጋር በጋብቻ ትኖር ነበር፡፡ ሁለቱም እግዚአብሔርን የሚፈሩ ደግ ሰዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ልጅ የላቸውም ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ሐና እያዘነች ታለቅስ ነበር፡፡ ምግብም አትመገብም ነበር፡፡ ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን "የባሪያህን መዋረድ ተመልከተህ ብታስበኝ ለባሪያህ ወንድ ልጅ ብትሰጥ ዕድሜውን ሁሉ አንተን ያገለግላል፡፡" በማለት ትጠይቀው ነበር፡፡

የሐናን ጸሎት እግዚአብሔር ሰማት፡፡ በወንድ ልጅም ማሕፀንዋ ተከፈተ፡፡ ስሙንም ሳሙኤል አሉት፡፡ ሐና እና ሕልቃና ለእግዚአብሔር የተሳሉትን ስለት ለመፈፀም ሳሙኤል ጡት በጣለ ጊዜ ወደ መቅደስ አመጡት፡፡ ለካህኑ ለዔሊ "እግዚአብሔር የለመንሁትን ልመናዬን ሰጥቶኛል፡፡ እኔም ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ፡፡ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል" ብላ ሕፃኑን ሰጠችው፡፡ ሳሙኤልም በመቅደስ በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት ሞገስ እያገኘ አደገ፡፡

ከዕለታት በአንድ ሌሊት ሳሙኤል ተኝቶ ሳለ የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማ፡፡ ዔሊ የጠራው መስሎት "እነሆኝ" አለ፡፡ ካህኑ ዔሊም "አልጠራሁህም ተመልሰህ ተኛ" አለው፡፡ ሳሙኤል ተመልሶ ተኛ፡፡ እግዚአብሔርም ደግሞ "ሳሙኤል ሳሙኤል" ብሎ ጠራው፡፡ ሳሙኤልም ወደ ካህኑ ዔሊ ሄዶ "አባቴ ሆይ እነሆኝ" አለ፡፡ ካህኑም "ልጄ ሆይ እኔ አልጠራሁህም፤ ተመልሰህ ተኛ" አለው፡፡ ሳሙኤል እግዚአብሔር ተገልጦለት ስለማያውቅ ነገሩን ማስተዋል አልቻለም ነበር፡፡ ስለዚህ ተመልሶ ተኛ፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ የእግዚአብሔር ድምፅ ሳሙኤልን ጠራ፡፡

እርሱም ተነሥቶ ወደ ዔሊ ሄደ፡፡ ካህኑ ዔሊ ግን እግዚአብሔር ብላቴናውን እንደጠራው አውቆ "ሄደህ ተኛ ቢጠራህም፡-

www.zeorthodox.org

አቤቱ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው" አለው፡፡

ሳሙኤል ሄዶ ተኛ፡፡ እግዚአብሔርም በሳሙኤል አጠገብ መጥቶ ቆመ፡፡ እንደ ቀድሞ "ሳሙኤል ሳሙኤል" ብሎ ጠራው፡፡ ሳሙኤልም "ባሪያህ ይሰማልና ተናገር" አለ፡፡ እግዚአብሔርም "በእስራኤል ላይ ቅጣት አመጣለሁ በዔሊም ቤት ላይ እፈርዳለሁ" አለው፡፡ ሳሙኤል እስኪነጋ ተኛ ማልዶም የሆነውን ሁሉ ለዔሊ ነገረው፡፡ ዔሊም "እርሱ እግዚአብሔር ነውና የወደደውን ያድርግ" አለ፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች እንደ ሳሙኤል ታዛዥ፣ ታማኝ፣ ቅንና ንጹሕ ልጆች ከሆናችሁ እግዚአብሔር ከጠቢባን የሰወረውን ለእናንተ ይገልጥላችኋል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ልጆች ከዚህ ምን ተማራችሁ?
2. የሳሙኤል እናት ማን ናት?
3. የሳሙኤል ወላጆች ሳሙኤልን ወደ መቅደስ ያመጡት ለምንድን ነው?
4. እግዚአብሔር ካህኑ ዔሊ እያለ ለምን ሕፃኑ ሳሙኤልን አናገረው?
5. ሳሙኤል ካደገ በኋላ ምን ሆነ?

## ተግባር

መምህሩ ለልጆቹ ጠዋትና ማታ እንዲጸልዩ፣ በሰንበተ ክርስቲያን ወደ ቤተክርስቲያን በመምጣት ቅዳሴ እንዲያስቀድሱና ቅዱስ ቁርባን እንዲቀበሉ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ መስቀል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የመስቀልን ታሪክና ጥቅም ለልጆች ማስተማር

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ” ገላ. ፮÷፲፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ ፶፱÷፬፣ ማቴ ፲፮÷፳፬ እና ኤፌ. ፪÷፲፮

**መግቢያ**

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ልጆች መስቀል ትሳለማላችሁ?
- ስለ መስቀል የምታውቁትን ለጓኞቻችሁ ንገሩ፡፡
- የምታውቋቸውን የመስቀል ዓይነቶች ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ስለ ንግሥት እሌኒ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ የሰማችሁትን አካፍሉን?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች በብሉይ ኪዳን መስቀል የወንበዴዎች መቅጫ ነበር፡፡ በሐዲስ ኪዳን ግን ጌታችን ኢየሱስ ከተሰቀለበት በኋላ መስቀል የድል አርማና የሰላም ምልክት ሆኗል፡፡ ስለዚህ የእኛ የክርስቲያኖች ምልክት የክርስቶስ መስቀል ነው፡፡

በአንድ ወቅት አይሁድ በቅናት ተነሣስተው ይህን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል ቀበሩት፡፡ ለሦስት መቶ ዓመታትም ዕፀ መስቀሉ ከክርስቲያኖች እይታ ተሰወረ፡፡ ብዙ ደጋግ አባቶች ስለ መስቀሉ መቀበር ያለቅሱ ነበር፡፡ እግዚአብሔር የልጆቹን እንባ የሚያብስበትና የጠላትን ምክር የሚያፈርስበት ጊዜ ደረሰ፡፡ እሌኒ የምትባል ደግ ሴት አስነሣ፡፡

እሌኒ የረዳትን እግዚአብሔርን የምታመልክ መልካም ሴት ናት፡፡ የክርስቶስን መስቀል ከተቀበረበት ለማውጣት ትፈልግ ነበር፡፡ ልጇ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስን “የጌታዬን መስቀል መፈለግ አለብኝ” አለችው፡፡ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስም ብዙ ገንዘብና ወታደሮች ሰጣት፡፡ እሌኒም የጌታን መስቀል ፍለጋ ወደ ኢየሩሳሌም መጣች፡፡ ስለ መስቀሉ ብዙ ሰዎችን ጠየቀች፡፡ መስቀሉ ያለበትን ስፍራ ግን የሚያውቅ አላገኘችም፡፡ በመጨረሻም ኪራኮስ የሚባል አረጋዊ አግኝታ መስቀሉ ስለተቀበረበት ተራራ ነገራት፡፡ ነገር ግን ከሦስቱ ተራሮች በማንኛው ውስጥ መስቀሉ እንዳለ አያውቅም ነበር፡፡ ወደ ተራራዎቹም በደረሱ ጊዜ የጌታ መስቀል ያለበትን ተራራ ለማወቅ፤ ደመራ አስደምራ ዕጣን ስታጨስ የዕጣኑ ጭስ መስቀሉ ወደተቀበረበት ተራራ ሰገደ፡፡

ንግሥት ዕሌኒ ጪሱ ባመለከተው ቦታ ተመርታ ልጇ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በሰጣት ወታደሮች ተራራውን አስቆፈረች፡፡



www.zeorthodox.org

ቁፈራው እንደተጠናቀቀ ሦስት መስቀሎችን አገኘች፡፡ የጌታ መስቀል የትኛው እንደሆነ ለማወቅም የሞተ ሰው አስመጥታ በመስቀሎቹ ላይ አስቀመጠች፡፡ የሞተው ሰው አስከሬን የጌታ መስቀል በነካው ጊዜ ተነሣ፡፡ እሌኒም በጣም ደስ አላት፡፡ ከልጇ ከቆስጠንጢኖስም ጋር ሆና ትልቅ ቤተክርስቲያን አነፀች፤ ቅዱስ መስቀሉንም በመቅደሱ በክብር እንዲቀመጥ አደረገች፡፡

## ማጠቃለያ

የጌታ ቅዱስ መስቀል ኃይላችን፣ ምልክታችን፣ መመኪያችንና አርማችን ነው፡፡ መስቀሉ ከሰይጣን ፈተናና ጥቃት የምንድንበት፤ ከክፉዎች ቀስት የምንጋረድበት ጋሻችን ነው፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. የንግሥት እሌኒ ልጅ የቁስጥንጥኒያ ንጉሥ ስሙ ማን ይባላል?
2. ለንግሥት እሌኒ መስቀሉ የተቀበረበትን ተራራ ያሳያት አረጋዊ ማን ነው?
3. የመስቀል ጥቅም ምንድን ነው?

## ተግባራት

- መምህሩ ልጆች በመስቀል ምልክት እንዲያማትቡ ያድርግ፡፡
- ልጆች የመስቀል ጸሎትና መዝሙራትን እንዲያጠኑ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# እረኛው ዳዊት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ለዳዊት ያደረገውን ጥበቃና ዳዊት ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር በጸሎትና በመዝሙር መግለፁን ለልጆች ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝም የለም፡፡" መዝ. ፳፫÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ሳሙ. ፲፯÷፴፬-፴፯፣ እና ሐዋ. ፲፫÷፳፪-፴፯

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ስለ ዳዊት ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- ዳዊት ምን ዓይነት ልጅ ነበር?
- ዳዊት የማን ልጅ ነው?
- ስለ ዳዊት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ዳዊት ከእሴይ ልጆች መካከል ታናሹ ነበር፡፡ በልጅነቱ በጣቶቹ በገና ይደረድር ነበር፡፡ ዳዊት ጸሎት ማድረግና መዘመር ይወድ ነበር፡፡ ዳዊት የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር፡፡ በጎችን ይንከባከባል፤ በለመለመ መስክ ያሰማራል፤ አውሬ እንዳይበላቸው ተግቶ ይጠብቃል፡፡ በአንድ ወቅት ከበጎቹ መሃል አንዷን በግ አንበሳ ነጠቀው፡፡ ዳዊትም አንበሳውን ተከትሎ መታው፤ የወሰዳትንም በግ ከአፉ አስጣለው ጉሮሮውን ይዞ መታና ገደለው፡፡ በጓንም ወደ መንጋዋ መለሰ፡፡ ዳዊት ጉልበት የሆነውን እግዚአብሔርን አመሰገነ፡፡ "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝ የለም፡፡" በማለት ዘመረ፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ለዳዊት ኃይል ሰጠው፡፡ ዳዊት አንበሳውን ገድሎ የወሰዳትን በግ አዳነ፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ኃይል ይሰጠናል፡፡ የሰጠንን ኃይል መልካም ነገር ብቻ ለመሥራት እንድናውለው ይፈልጋል፡፡

www.zeorthodox.org

## ***ጥያቄዎች***

1. የዳዊት የልጅነት ሥራ ምንድን ነበር?
2. ዳዊት አንበሳውን ለምን ገደለው?
3. ዳዊት አንበሳውን ከገደለ በኋላ ምን ብሎ ዘመረ?

## ተግባራት

- መምህሩ ልጆች መዝሙር ፳፪ በቃላቸው እንዲያጠኑና እንዲናገሩ ያድርግ፡፡
- “እግዚአብሔር እረኛዬ ነው” የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የዳዊት ለንጉሥነት መብቃት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ሰው የረሳቸውን እንደሚያስታውስና ታናናሾቹን በታላላቆች ላይ እንደሚሾም ለልጆች ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ" መዝ. ፳፪÷፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ሳሙ. ፲፮፣ ማቴ ፩÷፩ እና ራዕ. ፳፪÷፲፮

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ንጉሥ አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- የነገሥታት አለባበስ ምን ይመስላል? እስቲ ግለጹ?
- የንጉሥ ሥራ ምንድን ነው?
- ልጆች ንጉሥ መሆን ትፈልጋላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር ነብዩ ሳሙኤልን "ከእሴይ ልጆች መካከል ንጉሥ አዘጋጅቻለሁና በቀንድህ ዘይትን ሞልተህ ወደ ቤተልሔም ሰው ወደ እሴይ ቤት ሂድ" አለው፡፡ ሳሙኤልም ወደ እሴይ ቤት በመጣ ጊዜ ኤልያብን ተመልክቶ "በእውነት ይህ ንጉሥ ይሆናል" አለ፡፡ ኤልያብ ቁመቱ ረጅም መልኩ የሚያምር ነበርና፡፡ እግዚአብሔር ግን "ፊቱን የቁመቱንም ዘለግታ አትይ፤ ሰው ፊትን ያያል እኔ ግን ልብን አያለሁ" አለው፡፡ ኤልያብ ልቡ ውብ አልነበረም፡፡ ሳሙኤል እሴይን "ሌላ ልጅ አምጣ" አለው፡፡ እሴይም አሚናዳብን አቀረበ፡፡ ሳሙኤል "ይህንም እግዚአብሔር አልመረጠውም" አለው፡፡ እሴይ ሳማን በሳሙኤል ፊት አቆመ፡፡ ሳማንም እግዚአብሔር አልመረጠውም ነበር፡፡ እሴይ ከልጆቹ ሰባቱን በሳሙኤል ፊት አሰለፈ፡፡ ነቢዩ ሳሙኤልም "እነዚህን ሁሉ እግዚአብሔር አልመረጠልህም፤ ሌላ የቀረ ልጅ የለህምን?" አለው፡፡ እሴይም "ታናሹ ልጄ በጎች እየጠበቀ በሜዳ አለ፤ እርሱ ቀርቶአል" አለ፡፡ ሳሙኤልም "ልከህ አስመጣው" አለው፡፡ እሴይ እረኛው ዳዊትን አስጠራው፡፡ ዳዊትም መጣ፡፡ እግዚአብሔር ሳሙኤልን "ለንግሥና የመረጥኩት ይህ ነውና ተነሥተህ ቀባው" አለው፡፡ ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ ዳዊትን በወንድሞቹ መካከል ቀባው፡፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ በዳዊት ላይ በኃይል መጣ፡፡ ዳዊት ዓይኑ የተዋበ፤ መልኩ ያማረ ልቡ ቅን የሆነ መልካም ልጅ ነበር፡፡ የእስራኤልም ሁለተኛ ንጉሥ ሆነ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር እንደ ዳዊት የሚጸልዩ፣ የሚዘምሩ፣ ታዛዥ የሆኑና በቅንነት የሚያድጉ ልጆችን ይወዳል፡፡ ስለዚህ ይባርካቸዋል፤ በታላላቆችም ላይ ይሾማቸዋል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ዳዊትን እንዲቀባው የተላከው ነቢይ ማን ነበር?
2. ሳሙኤል ወደ እሴይ ቤት በደረሰ ጊዜ በመጀመሪያ ማንን ሊቀባ ነበር?
3. እግዚአብሔር ለምን ልብን ያያል?

## ተግባራት

1. መምህሩ ከልጆቹ መካከል አንዱ ይህን ታሪክ ለጓደኞቹ እንዲነግር ያድርግ፡፡
2. ወደፊት ምን መሆን እንደሚፈልጉ ይጠይቃቸው፡፡
3. የሚፈልጉትን ለመሆን ቀድመው መሆን ያለባቸውን ነገር ይንገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የጠፋው በግ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእግዚአብሔርን ፍቅርና ጥባቆት ለልጆች ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “መልካም እረኛ እኔ ነኝ” ዮሐ. ፲÷፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ. ፲፭፣ ሕዝ ፴፬ እና ዮሐ. ፲

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች በግ አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- ስለ በጎች አኗኗርስ መናገር ትችላላችሁ?
- እረኛ በጎቹን እንዴት አድርጎ ይጠብቃቸዋል?
- ስለ እስራኤል እረኞችና በጎች ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በጎች በጋራ ይመገባሉ፤ በጋራ ይኖራሉ፤ እረኛቸውን ከኋላ ይከተላሉ፤ የእረኛቸውን ድምፅ ለይተው ያውቃሉ፤ እረኛቸው ባሰማራቸው ቦታ ጸንተው ይገኛሉ፡፡ እረኛቸውም ቀበሮ እንዳይበላቸው፤ ተኩላ እንዳይጎዳቸው ተግቶ ይጠብቃቸዋል፡፡

መቶ በጎች ያሉት አንድ ሰው ነበረ፡፡ ከዕለታት በአንድ ቀን አንደኛው በግ ጠፋበት፡፡ ዘጠና ዘጠኙን በጎች በመሰማሪያቸው ትቶ የጠፋውን በግ ፍለጋ ሄደ፡፡ በመንገድ ያገኘውን ሰው ሁሉ “በጌን አያችሁትን?” እያለ በየሥፍራው ሁሉ ፈለገ፤ በጉንም አገኘው፡፡ ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ተሸከመው፡፡ ወደ ቤቱም አመጣው፡፡ ከዘጠና ዘጠኙ በጎች ጋር ጨመረው፡፡ ወዳጆቹንና ጎረቤቶቹን በአንድነት ተጠርቶ “የጠፋው በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ” አላቸው፡፡

ልጆች እረኛ የተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ መልካም እረኛ ነው፡፡ በጎች የተባልነው ደግሞ አዳምና ልጆቹ ነን፡፡ ዘጠና ዘጠኝ በጎች የተባሉት ዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት ናቸው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መላእክትን ትቶ አንዱን የጠፋውን አዳምን ፍለጋ ወደ ዓለም መጣ፡፡ አዳምን ከገነት ጫካዎች ጀምሮ እስከ ጎልጎታ ፈለገው፡፡ አገኘውም፡፡ ክርስቶስ አዳምን ባገኘው ጊዜ ደስ አለው፡፡ ውርደትን አስወገደ፤ በክብሩ አክብሮ፣ በቅድስናው ቀድሶ፣ በይቅርታውም በሕይወቱ ሞቱን ሽሮ ወደ ቀደመ ክብሩ መለሰው፤ ከቅዱሳን ኅብረት ደመረው፡፡ መላእክትም በጠፋው በአዳም መገኘት ደስ አላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ልጆች እኛ ዕድለኞች ነን፤ መልካም እረኛ አለን፡፡ እርሱም ሳያንቀላፋ ተግቶ የሚጠብቅ፤ ሳይደክም የሚሸከም፤ ከጠላት ቀስትና ከአውሬ የሚያድንና ነፍሱን ስለነፍሳችን የሰጠ እውነተኛ እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. የጠፋው በግ የማን ምሳሌ ነው?
2. መልካሙ እረኛችን ማን ነው?
3. እግዚአብሔር እንዴት ወደደን?

## ተግባሮት

- *መምህሩ ልጆች መዝሙር ሃያ ሁለትን በጋራ እንዲናገሩ ያድርግ፡፡*
- *መምህሩ ዮሐንስ ዐሥርን ያንብብላቸው፡፡*

www.zeorthodox.org

# ኢየሱስ ዐይነ ስውሩን አበራ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈዋሽ እንደሆነ ለልጆች ማሳወቅ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ሂድ እምነትህ አድኖሃል” ማር. ፲÷፶፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማር. ፲÷፵፮-፶፪ እና ሉቃ. ፲፰÷፴፭-፵፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ዐይነ ስውር ወይም ማየት የማይችል ሰው አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- ዐይነ ሥውር ምን የሚፈልግ ይመስላችኋል?
- ዐይነ ስውር ማለት ምን ማለት ነው?
- ልጆች ዐይነ ስውር እንዴት መሄድ ይችላል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በአንድ ወቅት ጌታ ኢየሱስ ከብዙ ሕዝብና ከደቀመዛሙርቱ ጋር ወደ ኢያሪኮ መጣ፡፡ የጤሜዎስ ልጅ ዐይነ ስውሩ በርጤሜዎስ እየለመነ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ነበር፡፡ ጌታችን ኢየሱስም በአጠገቡ አለፈ፡፡ በርጤሜዎስ የናዝሬቱ ኢየሱስ በአጠገቡ እንዳለፈ ባወቀ ጊዜ “የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ” እያለ ይጮህ ጀመር፡፡ ብዙዎችም ዝም እንዲል ገሥጹት፡፡ እርሱ ግን “የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ” እያለ እየጮኸ ተከተለው፡፡

ኢየሱስም ቆመና “ጥሩት” አለ፡፡ ዕውሩንም “አይዞህ ተነሣ የጠራኸው ይጠራሃል” ብለው ጠሩት፡፡ እርሱም እየዘለለ ተነሣና ልብሱን ጥሎ ወደ ኢየሱስ መጣ፡፡ ኢየሱስም “ምን ላደርግልህ ትወዳለህ?” አለው፡፡ በርጤሜዎስም “መምህር ሆይ አይ ዘንድ እወዳለሁ” አለው፡፡ ኢየሱስም በእጁ ዳሰሰውና “ሂድ እምነትህ አድኖሃል” አለው፡፡ ወዲያውም አየ ደስ ብሎት በመንገድም ተከተለው፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ልጆች ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን እንደሚችልና ከማንኛውም ችግር እንደሚያላቅቀን ብናምን የፈለግነውን ሁሉ ያደርግልናል፡፡

### ጥያቄዎች

1. ጌታችን ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ሆኖ ወዴት መጣ?
2. ኢየሱስ በኢያሪኮ መንገድ ዳር ማንን ፈወሰ?
3. በርጤሜዎስ ምንድን እንዲሆንለት ይፈልግ ነበር?

## ተግባር

ሩ መምህሩ ከልጆች መካከል አንዱ ይህን ታሪክ ለጓደኞቹ እንዲነግር ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ልጆች ክርስቶስን ተቀበሉ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ስለ ሆሳዕና በዓል ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሆሳዕና በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው" ዮሐ. ፲፪÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ. ፲፱÷፴፯-፵፣ ዮሐ. ፲፪÷፲፪-፲፯ እና መዝ. ፻፲፯÷፳፮

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ስለ ሆሳዕና በዓል አከባበር አመልካች ሥዕሎችን ያቅርብ፡፡
- ልጆች የሆሳዕና በዓልን አክብራችሁ ታውቃላችሁ?
- ልጆች ስለ ሆሳዕና መዝሙር ታውቃላችሁ? አንዱን መዝሙር መዘመር ትችላላችሁ?
- ልጆች የኢየሩሳሌም ሕፃናት ክርስቶስን ምን እያሉ አመሰገኑት?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደብረ ዘይት በሚባል ተራራ አጠገብ ወዳሉት ወደ ቤተፋጌ እና ወደ ቢታንያ በቀረበ ጊዜ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን ልኮ ማንም ያልተቀመጠባት አህያ ከነውርንጭላዋ አስመጣ፡፡ ደቀመዛሙርቱም በውርንጭላዋ ላይ ልብሳቸውን ጭነው ኢየሱስን አስቀመጡት፡፡ ሲሄድም ሕዝቡ ሁሉ ልብሳቸውን በመንገድ ያነጥፉ ነበር፡፡ የሚቀድሙትም የሚከተሉትም "ሆሳዕና በአርያም" እያሉ ይጮሁ ነበር፡፡ የኢየሩሳሌም ሰዎች የክርስቶስን መምጣት ሰሙ፡፡ ሕፃናትም የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው "በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፡፡ በሰማይ ሰላም በአርያም ክብር ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ" እያሉ እየዘመሩ ተቀበሉት፡፡ ፈሪሳውያን ግን ሕፃናት በማመስገናቸው ተበሳጭተው "ዝም አሰኛቸው ከልክላቸው" አሉት፡፡ ክርስቶስ ግን "ሕፃናት ዝም ቢሉ የቢታንያ ድንጋዮች ይጮሃሉ" አላቸው፡፡ እየተመሰገነ ወደ መቅደስ ገባ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

የኢየሩሳሌም አረጋውያንና ሕፃናት “ሆሳዕና በአርያም” እያሉ በደስታ ንጉሣቸው ክርስቶስን ተቀበሉት፡፡ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው “ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ” እያሉ ዘመሩለት፡፡ ልጆች የሚቀድሙ የተባሉ ነቢያትና የሚከተሉ የተባሉ ሐዋርያት ክርስቶስን አመስግነውታል፡፡ ያለፈው ትውልድ ለክብሩ ዘምሯል፤ ያለውና የሚመጣውም ትውልድ በዙፋኑ ሆኖ ዓለምን በፍቅርና በፍትሕ የሚመራውን ክርስቶስን ያመሰግናሉ እናንተም አመስግኑት፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ኢየሱስ ክርስቶስ በምን ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ?
2. ሕፃናት ምን እያሉ አመሰገኑት?
3. የሕፃናትን ምስጋና የተቃወሙት እነማን ናቸው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች የሆሳዕና መዝሙር በጋራ እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# መልአኩ የመቃብሩን ድንጋይ አንከባለለ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች የትንሣኤን ታሪክ እንዲያውቁ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ተነሥቷልና በዚህ የለም" ማቴ. ፳፰÷፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፳፰÷፩-፳፣ ሉቃ. ፳፬÷፩-፲፪ እና ሐዋ. ፪ እና ፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሰላቸው፡፡
- የክርስቶስን የትንሣኤ ሥዕል ለልጆች ያሳያቸው፡፡
- ልጆች ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- የትንሣኤ በዓልን ስታከብሩ ምን ታደርጋላችሁ?
- መላእክት ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ለደቀመዛሙርቱ ምን ሰበኩ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ኃጢአት በፈቃዱ በሥጋ ሞተ፡፡ ዮሴፍና ኒቆዲሞስም ቅዱስ ሥጋውን በአዲስ መቃብር አስቀመጡት፡፡ አይሁድም በትልቅ የቋጥኝ ድንጋይ መቃብሩን ዘጉ፡፡ በማኅተምም አተሙበት፡፡ የመቃብሩን ዙሪያ ወታደሮች ከበው መጠበቅ ጀመሩ፡፡ በሦስተኛው ቀን ኢየሱስ መቃብር ከፈቱልኝ፤ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ሞትን አሸንፎ ተነሣ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ በሌሊት ከተነሣ በኋላ ማርያም መግደላዊትና ሌሎች ሴቶች ወደ መቃብሩ መጡ፡፡ ክርስቶስ መነሣቱን እንዲያዩ የእግዚአብሔር መልአክ የመቃብሩን ድንጋይ አንከባሎ በላዩ ተቀምጦ ተመለከቱ፡፡ መልአኩ እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበር፡፡ ጠባቂ ወታደሮቹ መልአኩን ሲያዩ ደነገጡ፡፡ ማርያም መግደላዊትና ሴቶቹ ግን ወደ መልአኩ ቀረቡ፡፡ መልአኩም መልሶ "እናንተስ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁ፡፡ እርሱም እንደተናገረ ተነሥቷልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ሥፍራ ኑና እዩ" አላቸው፡፡

ማርያም መግደላዊትም ወደ ደቀመዛሙርቱ እየሮጠች ሄዳ "ደስ ይበላችሁ ጌታ ተነሥቷል" አለቻቸው፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቃብሩ ፈጥነው መጡ፡፡ ሴቶች እንደነገሯቸው መቃብሩ ባዶ ነበር፡፡ ክርስቶስም እንደተነሣ አመኑ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ልጆች ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን አሸንፎ የተነሣ የድል ጌታ ነው፡፡ መላእክቱ ያበሠሩን የምሥራችም ይህን ነው፡፡ የትንሣኤውን ነገር ከመላእክት የሰሙት ሴቶች ለደቀመዛሙርቱ ነገሩ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ተከተላቸው፡፡ የትንሣኤውም ወንጌል በኢየሩሳሌም ተሰበከ፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ልጆች ሞትን ድል የነሣው ማን ነው?
2. መልአኩ ለምን የመቃብሩን ድንጋይ አንከባለለ?
3. በማለዳ ወደ መቃብሩ የመጡት ሴቶች እነማን ናቸው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች በቃል የሚጠናውን ጥቅስ እንዲያስታውሱና የትንሣኤ መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ዮርዳኖስን ተሻገሩ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ሁልጊዜ በየትኛውም ሥፍራና ሁኔታ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደሆነ ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ተቀደሱ" መጽሐፈ ኢያሱ ፫፥፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ ኢያሱ ፫፥፩-፲፯፣ መዝ.፻፲፫፥፩-፰ እና ሮሜ.፰፥፴፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ወንዝ አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- ወንዝን እንዴት ማለፍ ይቻላል?
- ወንዝ ማየት ያስደስታችኋል?
- ስለ እስራኤላውያን የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት አውጥቶ በነጻነት ከፈርዖን ጽኑ አገዛዝ አውጥቶ በዕረፍት መራቸው፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ተስፋ ሰጣቸው፡፡ የሰጣቸውም ተስፋ ማርና ወተት የሞላበትን ምድረ ርስት ከነአንን ነበር፡፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲጓዙ እግዚአብሔር ባሕር ከፍሎ መና ከሰማይ እያወረደ ከዐለት ውኃ እያፈለቀ ምንም ሳያጎድል መራቸው፡፡

እስራኤላውያን የአርባ ዓመቱን ጉዞ አጠናቀው በተስፋይቱ ምድር አጠገብ ድንኳን ጣሉ፡፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገር አለባቸው፡፡ የዮርዳኖስ ወንዝ ደግሞ ሞልቶ ለእግረኞች አስቸግሮአል፡፡ በዋናም የሚታለፍ አይደለም፤ ኃይሉ አይሎአልና፡፡ እስራኤላውያን በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ሦስት ቀናት ተቀመጡ፡፡ ኢያሱም ሕዝቡን "ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ተቀደሱ" አላቸው፡፡ ካህናቱን ደግሞ "የቃልኪዳኑን ታቦት ተሸክማችሁ በሕዝቡ ፊት እለፉ" አለ፡፡

እግዚአብሔርም ኢያሱን "ከሙሴ ጋር እንደሆንሁ እንዲሁ ከአንተም ጋር መሆኔን ያውቁ ዘንድ በዚህ ቀን በእስራኤል ሁሉ ዓይን ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፡፡" ኢያሱም ሕዝቡን "ጠላቶቻችንን የወጋ የኤርትራን ባሕር ከፍሎ ያሻገረን እግዚአብሔር ዛሬም

በመካከላችሁ ነውና አትፍሩ” አላቸው፡፡

ሕዝቡ ሁሉ ዮርዳኖስን ሊሻገሩ ከድንኳን ወጡ፡፡ የቃልኪዳን ታቦት የተሸከሙት ካህናት በሕዝቡ ፊት ይሄዱ ነበር፡፡

ታቦት ተሸካሚዎቹ ወደ ዮርዳኖስ ሲደርሱ እግሮቻቸውን በውኃው ዳር አጠለቁ ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆመ ወራጁም ተቁዋረጠ፡፡ ሕዝቡም በኢያሪኮ ፊት ለፊት ተሻገሩ፡፡ የቃልኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ጸንተው ቆሙ፡፡ ሕዝቡ ሁሉ በደረቅ መሬት ዮርዳኖስን ተሻገሩ፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ነው፡፡ ሕዝቡን ባሕር ከፍሎ ይመራል፡፡ ሕፃናቱን ይጠብቃቸዋል፡፡ ልጆችን ያሳድጋል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ በቃል የሚጠናውን ጥቅስ ልጆች በጋራ እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ጴጥሮስ ጣቢታን አስነሣ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ተአምራት ማድረግን ለቅዱሳን እንደሰጠ ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል" ማቴ. ፲፱÷፳፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ ፱÷፴፮-፵፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?
- ልጆች ለቅዱሳን የተሰጣቸውን ክብርና ሥልጣን ታውቃላችሁ?
- ስለ ቅዱሳን የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ?
- ስለ ቅዱስ ጴጥሮስ አገልግሎት የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡
- ልጆች የጌታ ደቀመዛሙርትስንት ናቸው? ከደቀመዛሙርቱ መካከል በዕድሜ ትልቁ ማን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት

በኢዮጴ ጣቢታ የሚሏት አንዲት ሴት ነበረች፡፡ የስሟ ትርጉም ዶርቃ ማለት ነው፡፡ ጣቢታ ምጽዋት የምትመጸውት እና ደቀመዛሙርቱን የምታገለግል መልካም ሴት ነበረች፡፡

በአንድ ወቅት ታመመችና ሞተች፤ አጥበውም በሰገነት አኖሩአት፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ በልዳ አካባቢ እያገለገለ እንደሆነ ሰምተው እንዲያመጡት ሁለት ሰዎች ላኩ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር መጣ፤ አልዘገየምም፡፡ ወደ ኢዮጴም በደረሰ ጊዜ ወደቤት አምጥተው በሰገነት አወጡት፡፡ የሚያውቋትም መበለቶች ሁሉ እያለቀሱ ነበር፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስንም ባዩ ጊዜ ዶርቃ ትለብሳቸው የነበሩትን ልብሶች አሳዩት፡፡ ጴጥሮስም ሁሉም ወደ ውጭ እንዲወጡ አዘዘና ተንበርክኮ ጸለየ፡፡ ወደ ሬሳውም ዞር ብሎ "ጣቢታ ሆይ ተነሺ" አላት፡፡ እርስዋም ዓይኖቿን ከፈተች፡፡ ጴጥሮስንም ባየችው ጊዜ ተቀመጠች፡፡ እጁንም ዘርግቶላት አስነሣት፡፡ በሚያቋትም ሁሉ ፊት ሕያው ሆና ቆመች፡፡ ይህን የሰሙ ሁሉ በክርስቶስ አመኑ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ጴጥሮስ ሙሉ እምነት ስለበረው በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት በቆመ ጊዜ ጣቢታን ከሞት አስነሣት፡፡ በዚህም ተአምር ምክንያት ብዙዎች ክርስቲያን ሆኑ፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ጣቢታ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የጣቢታ ሃገር የት ነበር?
3. ቅዱስ ጴጥሮስ ጣቢታን ለማስነሣት ምን አደረገ?

## ተግባራት

- መምህሩ ልጆች ስለሕሙማን እንዲጸልዩ ያድርግ፡፡
- ሌሎች ቅዱሳን ያደረጉትን ተአምራት ይንገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# በዐለት ላይ የተሠራ ቤት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ የማድረግን ጥቅም ለልጆች ማሳወቅ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “እግዚአብሔር ዐለቴ ነው” መዝ. ፲፯÷፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፯÷፳፬-፳፯ እና ፩ቆሮ. ፲÷፩-፬

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ዐለት ታውቃላችሁ?
- ቤት ለመሥራት ምን ያስፈልጋል?
- የእግዚአብሔር ቃል ለምን ይጠቅመናል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰዎች ለተለያየ ዓላማ ይከተሉት ነበር፡፡ አንዳንዶቹ የሚያደርገውን ተአምራት ለማየት፤ አንዳንዶቹ የአንደበቱን ትምህርት ለመስማት፤ አንዳንዶቹ ደግሞ የሚያበረክተውን እንጀራ ለመብላት ይከተሉት ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን “ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚሉኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ አይደለም፤ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርጉ እንጂ” አላቸው፡፡

ስለዚህም ቃሉን ሰምቶ ማድረግ እንደሚገባ አስተማራቸው፡፡ ትምህርቱን በምሳሌ ለማስረዳት እንዲህ አላቸው፡፡ “ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ቤቱን በዐለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል፡፡ ዝናብ ወረደ፤ ጎርፍም መጣ፣ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንንም ቤት ገፋው፡፡ ነገር ግን በዐለት ላይ ስለተመሠረተ አልተናወጸም፡፡” አላቸው፡፡

ልጆች ቃሉን ሰምቶ የሚያደርገው ሰው በዐለቱ በክርስቶስ ላይ ሕይወቱን ይመሠርታል፡፡ የዓለም መከራ፣ ፈተና፣ ችግርና የሰይጣን ተንኮል ሊያነዋውጸው አይችልም፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተማሩን ቀጠለ፡፡ ቃሉን ሰምቶ ስለማያደርገው ሰው ምሳሌ መሰለ እንዲህ ብሎ፤ “ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል፡፡ ዝናብ ወረደ፤ ጎርፍም መጣ፤ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፤ ወደቀም አወዳደቁም ታላቅ ሆነ” አላቸው፡፡ ልጆች ቃሉን ሰምቶ በዐለቱ በክርስቶስ ላይ ያልተመሠረተ ሰው የዓለም መከራ፤ ፈተናና ስቃይ ያነዋውጸዋል፤ ሰይጣን ያሸንፈዋል፡፡ ምክንያቱም በዐለቱ ላይ ሕይወቱን አልመሠረተምና፡፡ ልጆች አሸዋ የዚህ ዓለም ሐሳብ፤ የሰው ሠራሽ ነገሮችና በእግዚአብሔር ላይ ያልታመነ ማንነትን ያሳያል፡፡ ስለዚህ ሰው በሰው ሠራሽ ነገሮች ሳይሆን በአምላኩ መደገፍ አለበት፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ልጆች ጠንካራ እምነት ያለው ሰው በዐለት ላይ ቤቱን የሠራ ሰውን ይመስላል፡፡ ስለዚህ በዐለታችን በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ የዓለምን መከራ እናሸንፋለን፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ዐለት ማን ነው?
2. አሸዋ የምን ምሳሌ ነው?
3. ቃሉን ሰምቶ የሚያደርገው ሰው ቤቱን በምን ላይ የመሠረተውን ሰው ይመስላል?

## ተግባር

*መምህሩ ልጆች በዐለትና በአሸዋ ላይ የተመሠረተ ቤት ሥዕል እንዲሠሩ ያድርግ፡፡*

www.zeorthodox.org

# አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔርን አምነው ተስፋ ለሚያደርጉት እንደሚጠነቀቅ ለልጆች ማስተማር

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሁሉም በልተው ጠገቡ" ማቴ. ፲፬÷፳

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፲፬÷፲፫-፳፩ እና መዝ. ፻፵፬÷፲፭

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እርቧችሁ ያውቃል?
- አምስት ሺሕ የተራበ ሕዝብ ለመመገብ ምን ያህል እንጀራ ያስፈልጋል?
- ልጆች ለተራበ ሰው አብልታችሁ ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ወቅት በታንኳ ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ አለ፡፡ ሕዝቡም ቃሉን ለመስማት ከከተማ ወጥተው በእግር ተከተሉት፡፡ ኢየሱስም ሕዝቡን አይቶ አዘነላቸው፡፡ ድውዮቻቸውንም ፈወሰ፡፡ የሕይወትንም ቃል አስተማራቸው፡፡ በመሸም ጊዜ ደቀመዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው፡- "ቦታው ምድረ በዳ ነው፤ አሁንም ሰዓቱ አልፏል፡፡ ወደ መንደሮች ሄደው ለራሳቸው ምግብ እንዲገዙ ሕዝቡን አሰናብት" አሉት፡፡

ኢየሱስም፡- "እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው እንጂ ሊሄዱ አያስፈልግም" አላቸው፡፡ ደቀመዛሙርቱም "ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ በቀር በዚህ የለንም" አሉት፡፡ ኢየሱስም "እነዚያን ወደዚህ አምጡልኝ" አላቸው፡፡ ሕዝቡንም በሳር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፡፡ አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ፡፡ እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀመዛሙርቱ ሰጠ፤ ደቀመዛሙርቱም ለሕዝቡ ሰጡ፡፡ ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ የተረፈውንም ቁርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሡ፡፡ ከሴቶችና ከልጆችም በቀር የበሉት አምስት ሺሕ ወንዶች ያህሉ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም እረኛ ነው፤ የሚያሳጣን የለም፤ የሚያስፈልገንን ሁሉ ያሟላልናል፡፡ እርሱን የሚከተሉትንና አምነው ተስፋ የሚያደርጉትን ምንም ሳያጎድል ይመራቸዋል፡፡

### ***ጥያቄዎች***

1. ጌታችን ኢየሱስ የመገበው ሕዝብ ብዛት ስንት ነበር?
2. ሕዝቡ ሁሉ ተመግበው የተረፈው ስንት ቅርጫት ሆነ?
3. ደቀመዛሙርቱ ለሕዝቡ ስንት እንጀራና ዓሣ አቀረቡ?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ከምግብ በፊትና በኋላ የእግዚአብሔርን ስም እንዲጠሩ ያለማምዳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የመክሊት ምሳሌ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጸጋ እንዲያውቁና እንዲጠቀሙበት ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አንተ መልካም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ" ማቴ. ፳፭÷፳፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፳፭÷፲፬-፴

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጸጋ ታውቃላችሁ?
- ችሎታችሁ ምንድን ነው?
- ከእናንተ መካከል መዘመር የሚችል አለ? ግጥም መጻፍ የሚችልስ? ሥዕል መሣል የሚችልስ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ወቅት ለደቀመዛሙርቱና ይከተለው ለነበረው ሕዝብ በምሳሌ ቃሉን ያስተምር ነበር፡፡ ልጆች ምሳሌያዊ ታሪኩ እንደሚከተለው ነውና በሚገባ ተከታተሉ፡፡ "ወደ ሌላ አገር የሚሄድ ንጉሥ ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ ለእያንዳንዳቸው እንደ አቅማቸው አከፋፈላቸው፡፡ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱ ሁለት ለአንዱም አንድ መክሊት ሰጠና "በሉ ሥሩበት" ብሏቸው ወዲያው ወደ ሌላ አገር ሄደ፡፡

አምስት መክሊት የተቀበለው ነገደበት ሌላ አምስት መክሊት አተረፈ፡፡ ሁለት የተቀበለውም እንዲሁ ሠርቶ ሌላ ሁለት አተረፈበት፡፡ አንድ የተቀበለው ግን ሄዶ ምድርን ቆፈረ፤ ጌታው የሰጠውን ገንዘብ ቀበረ፡፡

ከብዙ ዘመን በኋላ የእነዚህ ባሮች ንጉሥ መጣና ተቆጣጠራቸው፡፡ "በሰጠኋችሁ መክሊት ምን ሠራችሁበት?" ብሎ ጠየቃቸው፡፡ አምስት መክሊት የተቀበለው ባሪያ ወደ ንጉሡ ቀረበና "ጌታ ሆይ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ ሌላ አምስት መክሊት አተረፍሁበት" አለው፡፡ ንጉሡም "መልካም ባሪያ ነህ በጥቂቱ ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ ወደጌታህ ደስታ ግባ" አለው፡፡

ሁለት መክሊት የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ "ጌታ ሆይ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ ሌላ ሁለት መክሊት አተረፍሁበት" አለው፡፡ ንጉሡም "መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ፡፡ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ" አለው፡፡ አንድ መክሊት የተቀበለው ግን ንጉሡን እንዲህ አለው፡፡ "ጌታ ሆይ ካልዘራህበት የምታጭድ ካልበተንክበት የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንክን አውቃለሁና ፈራሁ፤ መክሊትህንም በምድር ቀበርሁት፤ እነሆ መክሊትህ" አለው፡፡ ንጉሡ

www.zeorthodox.org

ተቆጣ፡፡ ባሪያውን "አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ በጥቂቱ አልታመንከምና ለብዙ አልሾምህም" አለው፡፡ ሌሎች አሽከሮቹንም አስጠርቶ "መክሊቷን ውሰዱበት አስር መክሊትም ላለው ስጡት፤ ላለው ሁሉ ይጨመርለታል ከሌለው ግን ያው ያለው ይወሰድበታል፡፡ የማይጠቅመውን ባሪያ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት" አላቸው እነርሱም ንጉሥ እንዳለው አደረጉ፡፡

ልጆች ንጉሥ የተባለው እግዚአብሔር ነው፡፡ ለሁላችንም እንደ አቅማችን ጸጋ ሰጥቶናል፡፡ ይህን ችሎታችንን ተጠቅመን እርሱን የሚያከብር መልካም ሥራ ከሠራን ዳግም ሊፈርድ ሲመጣ ወደ ዘላለም ደስታ ያስገባናል፡፡ በሰጠን ጸጋ ካልሠራንበት ግን ይቀጣናል፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ጸጋ (ችሎታ) ሰጥቶአል፡፡ ለአንዱ የመዘመር፤ ለአንዱ የመጻፍ፤ ለአንዱ የማንበብ፤ ለአንዱ የመናገር፤ ለአንዱም የሥዕል ወዘተ ችሎታ ሰጥቷል፡፡ ይህን ጸጋችንን ራሳችንንና ሌሎችንም ለመጥቀም ሰጪውንም ለማስመስገን ልንሠራበት ይገባል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ልጆች አምስት መክሊት የተሰጠው ስንት አተረፈ?
2. አንድ መክሊት የተሰጠው ለምን ቀበረው?
3. ንጉሡ አንድ መክሊት የሰጠውን ለምን ቀጣው?
4. ልጆች ይህን ምሳሌ መስሎ በጸጋ ስለማትረፍ ያስተማረው ማን ነው?
5. ይህ ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ በየትኛው መጽሐፍ ተመዝግቧል?

## ተግባራት

- መምህሩ ልጆች ያላቸውን ጸጋ እንዲያውቁና እንዲያገለግሉበት ያበረታታቸው፡፡
- ከልጆቹ መካከል የሚዘምር ካለ ይጋብዝ፡፡

www.zeorthodox.org

# የእርሾው ምሳሌ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች በዙሪያቸው ላሉ ሰዎች መልካም እንዲሆኑና የክርስትናን አርአያነት እንዲከተሉና እንዲያድጉበት ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "መንግስተ ሰማያት እርሾን ትመስላለች" ማቴ. ፲፫÷፴፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፲፫÷፴፫ እና ሐዋ. ፪

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እርሾ ታውቃላችሁ?
- የእርሾ ጥቅም ምንድን ነው?
- ስለ እርሾ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ወቅት ለምድራውያን ሰማያዊ ምስጢር ነገራቸው፡፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምሳሌ አስተማራቸው፡፡ እንዲህ በማለት፤ "አንዲት ሴት ዳቦ ለመጋገር ሦስት መስፈሪያ ዱቄት በቡሃቃ አስቀመጠች፡፡ ሊጡን የሚያቦካ ትንሽ እርሾ ጨመረችበት፡፡ ትንሹ እርሾም ብዙውን ሊጥ አቦካላትና የሚጣፍጥ ዳቦ ጋገረች፡፡ ዳቦውንም ስታየው ደስ አላት፡፡ የእግዚአብሔርም መንግሥት እስኪቦካ ድረስ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሰወረችውን፤ ሊጡን ያቦካውን እርሾ ትመስላለች" አላቸው፡፡ ልጆች ትንሹ እርሾ ብዙውን ሊጥ እንዳቦካው አወቃችሁ? የእግዚአብሔርም መንግሥት በምድር ላይ ስትሰበክ ጥቂቶች ብቻ ተቀበሏት፡፡ ጥቂቶች ሐዋርያትና አርድእት ብዙዎችን ሰበኩ፡፡ ብዙዎችም ወደ ክርስትና መጡ፡፡ ዛሬ ቢሊዮኖች የእግዚአብሔርን መንግሥት ተቀብለው ይጠባበቋታል፡፡

## ማጠቃለያ

እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን ለሌሎች መልካም ማድረግ አለብን፡፡ ከሕዝብ የእኛን መልካም ሥራ አይተው በሰማያት ያለውን አባታችን እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ ብርሃናችን በሰው ፊት ይብራ፡፡

www.zeorthodox.org

## ***ጥያቄዎች***

1. መንግሥቱን በእርሾ መስሎ ያስተማረን ማን ነው?

2. ሴቲቱ ዳቦ ለመጋገር ስንት መስፈሪያ ዱቄት አዘጋጀች?

3. ዳቦው እንዲቦካ ምን አደረገችበት?

## ተግባር

 መምህሩ ልጆች ለጓደኞቻቸው ማድረግ ስላለባቸው መልካም ነገር አብራርቶ በስፋት ይንገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# አራት ሰዎች ሽባውን መሸከማቸው

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱና ለመልካም ነገር እንዳተባበሩ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል” መክ. ፬÷፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማር. ፪÷፩-፲፪

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች በጋራ የመሆን ጥቅም ምንድን ነው?
- ችግረኞችን በጋራ ሆናችሁ ረድታችሁ ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቅፍርናሆም ገብቶ በቤት እንደ ሆነ ተሰማ፡፡ በደጅ ያለው ስፍራ እስኪጠባቸው ድረስ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፡፡ ቃሉንም ይነግራቸው ነበር፡፡ አራት ሰዎችም አንድን ሽባ በጋራ ተሸክመው ወደ እርሱ አመጡለት፡፡ ስለ ሕዝቡ ብዛት ወደ ኢየሱስ ማቅረብ ቢያቅታቸው እርሱ ያለበትን የቤቱን ጣራ አነሡ፡፡ በነደሉት የቤቱ ጣራ አሳልፈው ሽባውን ወደ ክርስቶስ አቀረቡት፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በአራቱ ሰዎች እምነትና ኅብረት ተደነቀ፡፡

በአልጋ ያመጡትን ሽባ “አንተ ልጅ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ” አለው፡፡ ተነሥቶም ወዲያው አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ ፊት ወጣ፡፡ ስለዚህም ሰዎች ሁሉ ተገረሙና “እንዲህ ያለ ከቶ አላየንም” ብለው እግዚአብሔርን አከበሩ፡፡

ልጆች ክርስትና አንዳችን ለአንዳችን እንድናስብ ያስገድደናል፡፡ የአምልኮ ሥርዓታችንም በጋራ መሆንን ያስተምረናል፡፡ ልጆች ካህናት ቅዳሴ ሲቀድሱ አይታችኋል? በኅብረት ነው የሚያገለግሉት፡፡

## ማጠቃለያ

ክርስትና የመልካሞች ኅብረት ነው፡፡ ልጆች እርስ በርሳችን በመዋደድ በመልካም ነገር ልንተባበር ይገባል፡፡ ሁለትም ሦስትም ሆነን ለመልካም ሥራ በስሙ ስንሰበሰብ እግዚአብሔር ኅብረታችንን ሊባርክ በመካከላችን ይገኛል፡፡ ክርስቶስ አራት ሆነው የታመመ ወዳጃቸውን ያመጡትን ወጣቶች አይቶ ደስ አለው፤ ፈወሰላቸውም፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች***

1. ኢየሱስ እንዲፈውሰው አራት ሰዎች ያመጡትን ሽባ ያስገቡት በየት ነው?
2. ኢየሱስ አራቱን ሰዎች አይቶ ደስ ያለው በምናቸው ነው?
3. ኢየሱስ ሽባውን ምን አለው?

## ተግባር

☙ መምህሩ ልጆች በጋራ ሆነው ሕሙማንን እንዲጠይቁና ነዳያንን እንዲረዱ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የአስቴር ንግሥት መሆን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** *ታማኝነትን ለልጆች ማስተማር*

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አስቴር በሚያዩዋት ሁሉ ዓይን ሞገስ አገኘች ነበር" መጽሐፈ አስቴር. ፪÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** *መጽሐፈ አስቴር ፩ እና ፪*

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ንግሥት አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- የእንስት ነገሥታትን ስም ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡
- ንግሥት በራሷ ላይ ምን ትደፋለች? ምንስ ትለብሳለች?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በብሉይ ኪዳን አርጤክስስ የሚባል አንድ ንጉሥ በአንድ መቶ ሃያ አገሮች ነገሠ፡፡ አስጢን የምትባል ቆንጆ ሚስት ነበረችው፡፡ አርጤክስስ መኳንንት፣ ትልልቅ ባለሥልጣኖች፣ ወዳጅና ዘመድ የተገኙበት ትልቅ ግብዣ ነበረው፡፡ መልከ መልካሟን ሚስቱን ንግሥት አስጢንን እንዲያመጡለት ሰባት ጃንደረቦች ላከ፡፡ እርሷ ግን የንጉሡን ትእዛዝ ንቃ እምቢ አለች፡፡ ንጉሡም እጅግ ተቆጣ፡፡ ንጉሡ የዘመኑን ነገር ከሚያውቁት ጥበበኞች፣ ሕግንና ፍርድን ከሚያከናውኑት ጋር መክሮ ሌላ ሚስት ለማግባት ወሰነ፤ ንግሥትነትም ከእርሷ ለተሻለችው ይሰጥ አለ፡፡

በግዛቱ ሥር ባሉ አገሮች የሚኖሩ መልከ መልካም ሴቶች ተሰበሰቡ፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዷ የመርዶክዮስ የአጎት ልጅ አስቴር ነበረች፡፡ ንጉሡና የንጉሣዊው ቤተሰቦች ሴቶቹን ለማየት ወጡ፡፡ የሁሉም ዓይን አስቴር ላይ ቀረ፡፡ አስቴር በሚያዩዋት ሁሉ ዓይን ሞገስ አገኘች ነበርና፡፡

ንጉሥ አርጤክስስ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት አስቴር ወደ ንጉሡ ተወሰደች፡፡ ንጉሥ አርጤክስስም ከደናግላን ሁሉ አስቴርን ወደደ፤ እግዚአብሔር ውበት ሆኗት ነበርና ሞገስና መወደድን አገኘች የመንግሥቱ ዘውድ በራሷ ላይ ተደረገ፡፡ በአስጢንም ፋንታ ንግሥት ሆነች፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር አስቴርን ቆንጆ አድርጎ ፈጥሯት፤ በሰውም ሁሉ ፊት ሞገስ ሆኗት ስለነበር በአስጢን ፈንታ ንግሥት ሆነች፡፡ ሕዝቧንም ከጠላት ሴራ አዳነች፡፡ አስጢን ግን ታማኝ ስላልነበረች ከንግሥትነት ተሻረች፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. በአንድ መቶ ሃያ አገሮች ንጉሥ ሆኖ የተሾመው ማን ነው?
2. አስጢን ለምን ከንግሥትነት ተሻረች?
3. በአስጢን ፋንታ ንግሥት የሆነችው ማን ነች?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች የንግሥት ሥዕል እንዲሥሉና ስለ እንስት ነገሥታት የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የአስቴር ጥንካሬ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ልጆቹን እንደሚጠብቃቸውና ከክፉዎች ምክር እንደሚያድናቸው ለልጆች ማስተማር

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የምታምኑ በርቱ ልባችሁም ይጽና" መዝ. ፴፩÷፳፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ አስቴር ከ፫-፯

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች አስቴር ለንግሥትነት እንዴት ተመረጠች?
- አስቴር ከማን ወገን ናት?
- አስቴርን ያገባት ንጉሥ ማን ይባላል?
- አስቴር ለንግሥትነት እንድትታጭ ያመጣት ማን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አስቴር ከእግዚአብሔር ሕዝብ ከእስራኤል ዘር የተገኘች ሴት ስትሆን አሕዛባዊውን ንጉሥ አግብታ ንግሥት ሆነች፡፡ ሐማ የሚባል አንድን ክፉ ሰው ንጉሡ አርጤክሰስ ከፍ ከፍ አደረገው አከበረውም፡፡ በንጉሡ በር ያሉ ባሪያዎች ሁሉ ለሐማ ሰገዱ፤ መርዶክዮስ ግን አልተደፋም፤ አልሰገደለትም ነበር፡፡ ሐማ በዚህ ምክንያት እጅግ ተቆጣ፡፡ በአርጤክሰስ ግዛት ያሉትን የመርዶክዮስን ወገኖች አይሁድን ሊያጠፋ ተንኮል ጠነሰሰ፡፡ ወደ አርጤክስስ መጥቶ "በምትገዛው ሕዝብ መካከል የተለየ ሕግ ይዘው የሚኖሩ የንጉሥን ሕግ የማይጠብቁ እስራኤላውያን አሉ" አለ፡፡ አርጤክስስም ቀለበቱን ከእጁ አወለቀ፡፡ ለሐማም ሰጠውና "የፈለከውን ነገር ታደርግባቸው ዘንድ ትችላለህ" አለው፡፡

ሐማም እስራኤልን የሚያጠፋ ዓዋጅ በንጉሡ ቀለበት አትሞ በአንድ መቶ ሃያ አገሮች በተነ፡፡ መርዶክዮስም የተደረገውን ሁሉ ባወቀ ጊዜ ልብሱን ቀደደ፤ ማቅም ለበሰ፤ አመድም ነሰነሰ፡፡ ወደ ከተማይቱም መካከል ወጥቶ ታላቅና የመረረ ጩኸት ጮኸ፡፡ ደብዳቤውም በደረሰበት አገር ሁሉ ታላቅ ሐዘንና ጾም፣ ልቅሶና ዋይታም ሆነ፤ ብዙዎችም ማቅ ለበሱ አመድ ነሰነሱ፡፡ መርዶክዮስ ለአስቴር መልእክተኞችን ላከ፡፡ አስቴርም ከመርዶክዮስ የተላከላትን መልእክት በሰማች ጊዜ እጅግ አዘነች፡፡ መርዶክዮስም "ንጉሡን ለምኚልን" አላት፡፡ አስቴር ግን "እንዴት ወደ ንጉሡ እገባለሁ? አልተጠራሁም" አለችው፡፡

መርደክዮስ ግን "በንጉሥ ቤት ስለሆንሽ ከአይሁድ ሁሉ እድናለሁ ብለሽ በልብሽ አታስቢ፡፡ በዚህ ጊዜ ቸል ብትይ ዕረፍትና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ስፍራ ይሆናል፤ እግዚአብሔር ወደ መንግሥት ያመጣሽ እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆነ ማን ያውቃል?" አላት፡፡

አስቴርም ለመርዶክዮስ "ሂደህ በሱሳ ያሉትን አይሁድ ሁሉ ሰብስብ ለእኔም ጹሙ ሦስት ቀን፣ ሌሊቱንና ቀኑን አትብሉ አትጠጡም፤ እኔና አገልጋዮቼም እንጾማለን፤ ምንም እንኳ ያለ ሕግ ቢሆን ወደ ንጉሡ እገባለሁ ብጠፋም እጠፋለሁ" ብላ ላከችበት፡፡ ንግሥት አስቴር እጅግ ጠንካራና ልባም ሴት ስለሆነች የንጉሡን ፊት የምታይበትን ብልሃት አሰበች፡፡ ጾምዋን እንደፈጸመች ልብሰ መንግሥቷን ለብሳ በንጉሡ ቤት በውስጠኛው ወለል ቆመች፡፡ ንጉሡም ከዙፋኑ ሆኖ አስቴርን አያት፤ በዓይኑም ሞገስ አገኘች፡፡ በእጁ የነበረውን የወርቁን ዘንግ ለአስቴር ዘረጋላት፡፡ አስቴርም ቀርባ የዘንጉን ጫፍ ነካች፡፡ ንጉሡም "ንግሥት አስቴር ሆይ የምትለምኚኝ ምንድ ነው?" አላት፡፡ አስቴርም "ለንጉሤ ግብዣ አዘጋጅቻለሁና ንጉሥ መልካም ሆኖ ቢታየው ከሐማ ጋር ወደ ግብዣዬ ይምጣ" አለችው፡፡ ንጉሡም በሐሳቧ ተስማማ፡፡

በግብዣው ዋዜማ ሐማ መርዶክዮስን ቁመቱ ሃምሳ ክንድ በሆነ ግንድ እንዲሰቅሉት አዝዞ ወደ ግብዣው ሄደ፡፡ ንጉሡ በዚያ ሌሊት እንቅልፍ አልወሰድ አለው፡፡ የዘመኑንም ታሪክ መጽሐፍ ያመጡ ዘንድ አዘዘ፡፡ በንጉሥም ፊት መጽሐፉ ተነበበ፡፡ መርዶክዮስ ንጉሡን ከሞት ያዳነበት ታሪክ ተገኘ፡፡

ንጉሡም "ስለዚህ ነገር ለመርዶክዮስ ምን ክብርና በጎነት ተደረገለት?" አለ፡፡ አገልጋዮቹም ምንም እንዳልተደረገለት ነገሩት፡፡ ንጉሡ ሐማን አስጠርቶ "ንጉሡ ሊያከብረው ለሚወደው ሰው ምን ይደረግለታል?" አለው፡፡ ሐማም ንጉሥ እርሱን የሚያከብረው መስሎት "ንጉሥ ያከብረው ዘንድ ለሚወድደው ሰው ንጉሡ የለበሰውን የክብር ልብስ፣ ንጉሥ የተቀመጠበትን ፈረስ፣ የንጉሡም ዘውድ ይሰጠው" አለው፡፡ ንጉሥ አርጤክስስ ሐማን "ፍጠን እንደተናገርከው ልብሱንና ፈረሱን ውሰድ በንጉሡ በር ለሚቀመጠው አይሁዳዊ ለመርዶክዮስ እንዲሁ አድርግለት ከተናገርኸው ሁሉ ምንም አይቅር" አለው፡፡

ሐማ ግን በልቡ አዘነ መርዶክዮስ እንዲገደል መክሮ ነበርና፡፡ ንጉሥ ያዘዘው መሆን ስላለበት ለመርዶክዮስ ከተናገረው አንዳች ሳያስቀር እንደ ቃሉ አደረገለት፡፡ ንጉሡና ሐማ ወደ ንግሥት አስቴር ግብዣ መጡ፡፡ ግብዣውም ሲጠናቀቅ አስቴር በንጉሡ ፊት ቆመች፡፡ ንጉሡም "የምትፈልጊውን ጠይቂኝ" አላት፡፡ አስቴርም "ንጉሡን ደስ ቢያሰኘው ሕይወቴ በልመናዬ ሕዝቤም በመሻቴ ይሰጠኝ፤ በእኔና በሕዝቤ ሞት ታውጆብናል፡፡ ባሪያዎች ልንሆን ተሸጠን እንደ ሆነ ዝም ባልሁ ነበር፤ የሆነ ሆኖ ጠላቱ የንጉሡን ጉዳት ለማቅናት ባልቻለም" አለች፡፡ ንጉሥ አርጤክሰስ "ይህን ያደርግ ዘንድ በልቡ የደፈረ ማን ነው?" አለ፡፡ አስቴርም "ሐማ ነው" አለችው፡፡ ንጉሡ ሐማ ለመርዶክዮስ በተዘጋጀው ግንድ እንዲሰቀል አዘዘ፡፡ አይሁዳውያንንም ነጻ የሚያወጣ ዓዋጅ በቀለበቱ አትሞ በመቶ ሃያ የግዛቱ አገሮች አስላከ፡፡

## ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ሕዝብ በጠላት ምክር አይጎዱም፡፡ እረኛቸው እግዚአብሔር ተግቶ ይጠብቃቸዋልና፡፡ ልጆች የማይተኛ፣ የማያስነካና በለምለም መስክ የሚያሰማራ እረኛ እንዳለን እወቁ፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች***

1. ሐማ መርዶክዮስን የጠላው ለምንድን ነበር?
2. አስቴር ሕዝቡን ለማዳን ምን አደረገች?
3. የመርዶክዮስ ውለታ ምንድን ነበር?
4. አይሁዳውያን በመጾማቸው ምን ተጠቀሙ?
5. የክፉው የሐማ ፍጻሜ ምንድን ነበር?

# ተግባር

ᏋᏋ መምህሩ ከልጆች መካከል አንዱ ይህን ታሪክ ደግሞ እንዲተርክ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ደግ ሩት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** አረጋውያንን ማክበርና መደገፍ እንደሚገባ ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ልጄ ሆይ **በእግዚአብሔር** የተባረክሽ ሁኚ ቸርነትን አድርገሻልና” መጽሐፈ ሩት. ፫÷፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ ሩት ከ፩-፬

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች አያቶች አሏችሁ?
- ትታዘዙአቸዋላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በሞአብ አገር ኑኃሚን የምትባል አንዲት ቤተልሔማዊት ሴት ትኖር ነበር፡፡ ባሏ አቤሜሌክ ሞተባት፡፡ ኬሌዎንና መሐሎን የሚባሉ ሁለት ልጆች ነበሯት፡፡ ሁለቱ ልጆቿ ሩትና ዖርፋን አገቡ፡፡ ከዐሥር ዓመት በኋላ መሐሎንና ኬሌዎን ሞቱ፡፡ ቤተልሔማዊቷ ኑኃሚን ብቻዋን ቀረተ፡፡ ኑኃሚን ዕድሜዋ እየገፋ ስለሄደ አረጀች፡፡

በአንድ ወቅት ቤተልሔምን እግዚአብሔር እንደጎበኛት ሰማች፡፡ ሁለቱንም ምራቶቿን ሩትና ዖርፋን ጠርታ፡- “ወደ እናቶቻችሁ ቤት ተመለሱ፤ በእኔና በሞቱት እንዳደረጋችሁ እግዚአብሔር ቸርነት ያድርግላችሁ፡፡ እኔም ወደ ቤተልሔም እመለሳለሁ” አለቻቸው፡፡

ዖርፋ ወደ ወገኗ ተመለሰች፡፡ ሩት ግን “ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል ከአንቺ አልለይም” በማለት ከኑኃሚን ጋር ወደ ቤተልሔም መጣች፡፡ ኑኃሚን እና ሩት በቤተልሔም አዲስ ኑሮ ጀመሩ፡፡ ሩት አሮጊቷን ኑኃሚንን ለመንከባከብ ቃርሚያ ትለቅም ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ቦኤዝ በሚባል ኃያል ሰው እርሻ ቃርሚያ ስትቃርም ዋለች፡፡ ቦኤዝም ለቤተልሔም እንግዳ እንደሆነች አውቆ “ይህች የማናት ቆንጆ?” በማለት ጠየቀ፤ ወደ እርሱም አቅርቦ “ቃርሚያ ለመቃረም ወደ ሌላ እርሻ አትሂጂ ገረዶቼን ተጠጊ” አላት፡፡ ቦኤዝ የራሷ ባልሆነ ምድር ኑኃሚንን ለመንከባከብ በመጣችው በሩት ደግነት ተገረመ፡፡ ቸርነትም አደረገላት፡፡

ሩት ወደ ኑኃሚን በመጣች ጊዜ የሆነውን ሁሉ ነገረቻት፡፡ ኑኃሚንም ለሩት ስለቦኤዝ ደግነት ነገረቻት፡፡ በመጨረሻም ሩትና ቦኤዝ በጋብቻ መኖር ጀመሩ፡፡ እግዚአብሔርም ሩትን ስለደግነቷ ባረካት፡፡ የዳዊትም ቅድመ አያት ሆነች፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ልጆች ለአረጋውያን በምናደርገው ደግነት፤ እግዚአብሔር ይባርከናል፡፡ አረጋውያንን በሚያስፈልጋቸው መልካም ነገር ሁሉ መታዘዝ፣ መርዳትና መንከባከብ ይገባናል፡፡ ለአረጋውያን መልካም ነገርን የሚያደርጉ ልጆችን እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜን ያጠግባቸዋል፡፡ ልጆች አረጋውያንን አክብራችሁ ታዘዙአቸው እንጂ አታቃሏቸው፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ሩት የተባረከችው ማንን በመርዳቷ ነው?
2. ሩት ትቃርምበት የነበረው እርሻ የማን ነው?
3. ሩት ማንን ወለደች?
4. ኑኃሚን የእነማን እናት ናት?
5. የሩት አገር የት ነበር?

## ተግባር

- መምህር ልጆች አረጋውያንና አያቶቻቸውን እንዲታዘዙና እንዲያከብሯቸው ይምከሯቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# በለዓምና አህያው

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእንስሳትን ደኅንነት መጠበቅና መንከባከብ እንደሚገባ ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የሌላውን መከራ ለእናንተ እንደሚሆን አድርጉ" ፩ ጴጥ. ፫÷፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘኁልቁ. ፳፪፣ ፪ጴጥ ፪÷፲፭ እና ራዕ. ፪÷፲፬

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የአህያን ሥዕል መሥራት ትችላላችሁ?
- የአህያ አገልግሎት ምንድን ነው?
- ልጆች አህያ መናገር ትችላለችን?
- በምድር ከሚኖሩ ፍጥረታት መናገር የሚችለው ማን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በለዓም ነቢይ ነው፡፡ አንዲት አህያ ነበረችው፡፡ በአንድ ወቅት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስለ ባላቅ ምክርና አምሃ ሊረግም አህያይቱን ጭኖ ከሞአብ አለቆች ዘንድ ሄደ፡፡ በዚህም እግዚአብሔር ተቆጣ፤ እንዲቋቋመውም መልአኩን ላከ፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ በለዓምን ሊቋቋም በመንገድ ላይ ቆመ፡፡ አህያይቱም የእግዚአብሔርን መልአክ በመንገድ ቆሞ የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ ይዞ አየችው፡፡ ከመንገዱ ፈቀቅ ብላ ወደ እርሻው ውስጥ ገባች፡፡ በለዓም ወደ መንገድ ሊመልሳት አህያይቱን መታት፡፡ አህያይቱ ግን በፊቷ የተመዘዘ ሰፍይ ይዞ የቆመውን ሰማያዊ መልአክ ስላየች መሄድ አልቻለችም፤ በለዓም ደጋግሞ አህያይቱን ደበደባት፡፡ መልአኩ በፊቷ ስለቆመ መሄድ አልቻለችምና ከበለዓም እግር ሥር ተኛች፡፡ በለዓም በአህያይቱ ድርጊት እጅግ ተቆጥቶ አህያይቱን በጣም ደበደባት፡፡ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የአህያይቱን አፍ ከፈተና፡፡ በለዓምን በሰው ቃል መናገር ጀመረች፡፡ "የምትመታኝ ምን አድርጌህ ነው?" አለችው፡፡ በለዓምም "ስላላገጥሽብኝ ነው፤ በእጄ ሰይፍ ቢኖር አሁን በገደልኩሽ ነበር" አላት፡፡ አህያይቱ በለዓምን "ከብዙ ዘመን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የምትቀመጥብኝ አህያ አይደለሁምን? እስከአሁን እንዲህ አድርጌ አውቃለሁ?" አለችው፤ "እንዲህ አላደረግሽም" አላት፡፡ እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ፡፡ የእግዚአብሔርን መልአክ በመንገድ ላይ የተመዘዘ ሰይፍ በእጅ ይዞ አየ፡፡ በለዓም ለመልአኩ ሰገደ በግምባሩም ወደቀ፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ "ለምን አህያይቱን ሦስት ጊዜ መታህ? መንገድህ በፊቴ ጠማማ ነውና እቋቋምህ ዘንድ መጣሁ፡፡ አህያይቱ አይታኝ ከእኔ ፈቀቅ አለች፤ በፊቴ ፈቀቅ ባላለች በእውነት በገደልኩህ ነበር" አለው፡፡ በለዓምም ጥፋቱን አመነ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ከአንደበቷ ቃል አውጥታ መናገር የማትችለውን አህያ እግዚአብሔር እንድትናገር አድርጎ የነቢዩን እብደት አግዷል፡፡ ልጆች አህያዋ ምንም ሳትበድል መመታቷ አግባብ አይደለም፡፡ ለእርሱ አልታይ ያለውን መልአክ አይታ በመንገድ ቆመች እንጂ አልሰነፈችም፡፡ እንስሳትን መንከባከብና ደኅንነታቸውን መጠበቅ ይገባል፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ "ለምን መታሃት" ብሎ በለዓምን ገሥጾታልና፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. የበለዓም አህያ በመንገድ ላይ የቆመችው ለምንድን ነው?
2. የበለዓም አህያ እንዴት መናገር ቻለች?
3. መልአኩ በለዓምን ሊቋቋመው የመጣበት ምክንያት ምንድን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆቹን ለእንስሳት ደኅንነት ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያደርጉ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የእመቤታችን የማርያም ልደት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት ለመሆን ስለመመረጧ ልጆች በቂ ዕውቀት እንዲያገኙ ማስቻል፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደቃልህ ይደረግልኝ" ሉቃ. ፩÷፴፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃስ ፩÷፳፮-፶፮ እና ተአምረ ማርያምና ነገረ ማርያም፡፡

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በሐዲስ ኪዳን ዋዜማ ኢያቄምና ሐና የሚባሉ መልካም ባለትዳሮች ነበሩ፡፡ ሁለቱም ልጅ ስለሌላቸው እያዘኑ ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ነበር፡፡ መልካም ልጅ እንዲሰጣቸው ይለምኑት ነበር፡፡

በአንድ ወቅት ኢያቄም ሊጸልይ ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ወጣ፡፡ ለጸሎትም በቆመ ጊዜ የእግዚአብሔርን መልአክ አየ፡፡ የእግዚአብሔር መልአክም "ኢያቄም ሆይ አትፍራ እግዚአብሔር ልጅ ይሰጥሃልና አትዘን" አለው፡፡ ኢያቄም ደስ እያለው ወደ ቤቱ ተመለሰና ለሐና ነገራት፡፡ ሐናም በሰማችው ነገር በጣም ደስ አላት፡፡ ለእግዚአብሔርም ቃል ገባች፡፡ "አምላኬ ሆይ እንደ ቃልህ ልጅ ስጠኝ እንጂ ወንድ ቢሆን ካህን ሆኖ እንዲያገለግልህ፤ ሴት ብትሆን ደግሞ በመቅደስህ ሐር እና ወርቅ እያስማማች እንድታገለግልህ የሰጠኸኝን መልሼ እሰጥሃለሁ" አለች፡፡

እግዚአብሔር ለኢያቄምና ለሐና ሐምሌ ሠላሳ ቀን ሕልም አሳያቸው፡፡ ሐናም ነሐሴ ሰባት ቀን እመቤታችን ማርያምን ፀነሰች፡፡ ግንቦት አንድ ቀን በሊባኖስ ተራራ ወለደች፡፡ ስሟንም ማርያም አሏት፡፡ ሦስት ዓመት በሞላት ጊዜ ልጃቸውን ወደ እግዚአብሔር መቅደስ አምጥተው ለካህኑ ዘካርያስ ሰጧት፡፡ መልአኩ ፋኑኤል ኅብስተ ሰማይ በክንፎቹ ጋርዶ መገባት፡፡ ሐርና ወርቁን እያስማማች በመቅደስ አደገች፡፡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተልኮ መጣና፤ "ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ደስ ይበልሽ" በማለት የአምላክ እናት ለመሆን እንደተመረጠች አበሠራት፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ልጆች እግዚአብሔር የእመቤታችን የማርያምን ትሕትናዋን ወደደ፡፡ ማደሪያውም ትሆን ዘንድ መረጣት፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የእግዚአብሔርን ፈቃድ የፈጸመች ቃሉን ያመነች፤ አካላዊ ቃልን የወለደች ብፅዕት እናት ናት፡፡ ስለዚህ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሏታል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ልጆች እመቤታችን የማርያም እናትና አባት እነማን ናቸው?
2. የእመቤታችን ማርያም የልደት ቀን መቼ ነው?
3. እመቤታችን ማርያም የማን እናት ናት?
4. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ትውልድ ሁሉ ምን ይላታል?
5. እመቤታችን ማርያምን ያበሠራት መልአክ ማን ይባላል?

## ተግባራት

- መምህሩ ከልጆች መካከል አንዱ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተማሩትን እንደገና እንዲተርክ ያድርግ
- ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልደት መዝሙር በጋራ እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ፍቅር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ወደ ቤተክርስቲያን መሄድን እንዲወዱና እንዲናፍቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ" መዝ. ፭÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ሳሙ ፫÷፩፣ ፩ነገ. ፰ እና ሉቃ ፲፱÷፵፭

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ወደ ቤተክርስቲያን ስትመጡ ደስ ይላችኋል?
- "ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ" ያለ ንጉሥ ማን ነው?
- ልጆች በቤተ መቅደስ ያደጉ የእግዚአብሔር ሰዎች እነማን ናቸው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤተመቅደስ ሲገባ ነጋዴዎች ሲሸጡና ሲለውጡ አገኛቸው፡፡ በጣም ተቆጣ ጅራፍም አበጅቶ እንስሳቱን እየገረፈ አስወጣ፡፡ ሻጪና ለዋጮቹንም "የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት ቤቴ የጸሎት ቤት ናት" በማለት ገሠጻቸው፡፡ ልጆች ከዚህ ታሪክ ውስጥ ምን ተማራችሁ? ቤተክርስቲያንን ማክበር እንደሚገባ፤ ቤቱን የማያከብሩትን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚቀጣቸው ያስተምራል አላችሁ? ጎበዝ ልጆች፡፡ ስለዚህ ልጆች ወደ ቤተክርስቲያን ስንመጣ ማድረግ ስላለብን ነገር እንማር፡፡

***ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ***

- ነጠላችንን አመሳቅለን እንለብሳለን፡፡
- የቤተክርስቲያን በር ላይ ስንደርስ ፊታችንን በትምህርተ መስቀል እናማትባን፡፡
- በቅድስናው መቅደስ ፊት እንሰግዳለን፡፡
- ጫማችንን አውልቀን በምሕረቱ ብዛት ወደ ቤቱ እንገባለን፡፡
- እንቅስቃሴያችን ሁሉ በጸጥታና በእርጋታ መሆን አለበት፡፡
- መስቀል እንሳለማለን፤ ጠበል እንጠጣለን፤ ቃሉን እንሰማለን፡፡
- በቅዳሴ ጊዜ የአምላካችንን ቅዱስ ሥጋና ደም እንቀበላለን፡፡
- ለአባታችን ለእግዚአብሔር ሰግደን፤ መንገር የምንፈልገውን በጸሎት ነግረን ወደ ቤታችን እንመለሳለን፡፡



www.zeorthodox.org

- ካህን ስናይ ወደ ካህኑ ዘንድ ሄደን መስቀሉን መሳለም እና “ይጸልዩልኝ” ማለት አለብን፡፡

ልጆች በቤተ ክርስቲያን ማድረግ የሌለባችሁን ታውቃላችሁ?

***ልጆች ወደ ቤተ ክርስቲያን ከገባን በኋላ፡-***

- ከጓደኞቻችን ጋር መጫወትና ማውራት
- በዐውደ ምሕረትና በቤተመቅደስ ውስጥ፣ በቅዳሴና በስብከተ ወንጌል ጊዜ ምግቦችንና መጠጦችን መብላትና መጠጣት
- በቅዳሴ ጊዜ መግባትና መውጣት
- ጮኸን ሌሎችን መረበሽ የለብንም፡፡

# ማጠቃለያ

ልጆች ቤተ ክርስቲያንን የምንወዳት የእግዚአብሔር ቤት ስለሆነች ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝባት፣ የጸሎት፣ የሰላም፣ የድኅነት፣ የበረከት ቦታ ነች፡፡ በጥምቀት የእግዚአሔርን ልጅነት የምናገኝባት፤ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን የምንቀበልባት ወንጌልን የምንማርባት የድኅነት ቤታችን ነች፡፡ ስለዚህ በመልካም አረማመድ በእግዚአብሔር ቤት ብናድግ እግዚአብሔር ይባርከናል፡፡

***ጥያቄዎች***

- ልጆች ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ምን ማድረግ አለብን?
- ልጆች በቤተክርስቲያን ማድረግ የሌለብን ምንድን ነው?
- ቤተ ክርስቲያንን የምንወዳት ለምንድን ነው?

# ተግባራት

- መምህሩ፤ ልጆች በቤተክርስቲያን የሚጸልዩትን ጸሎት ያስተምራቸው፡፡
- በቅዳሴ ጊዜ ማድረግ ያለባቸውን ይንገራቸው፡፡
- ልጆች የቤተክርስቲያን ሥዕል እንዲሠሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# መልአኩ ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር ቤት ነጻ አወጣው

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር እንደሚወደንና ለጸሎታችን ምላሽ ቶሎ እንደሚሰጠን ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "መልአኬን በፊትህ እሰድዳለሁ" ዘፀ. ፳፫÷፳

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፲፪÷፩-፲፯ እና መዝ. ፴÷፩-፲

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የመላእክት ሥራ ምንድን ነው?
- መላእክት ወደ እኛ የሚላኩት ለምንድን ነው?
- ቅዱስ ጴጥሮስ ማን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱስ ጴጥሮስ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ነው፡፡ ጌታችንን ይወድ የነበረ የትንሣኤው ምስክር ነው፡፡ ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኢየሩሳሌም እየተዘዋወረ ለብዙዎች ያስተምር ነበር፡፡ ንጉሥ ሄሮድስ ይህን በስማ ጊዜ ተቆጣ፡፡ ወታደሮቹን ልኮ ያዕቆብን አስገደለ፤ ጴጥሮስን በእስር ቤት እንዲታሰር አደረገው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ግን አልፈራም፡፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሆነ ያምናልና "መልአኬን በፊትህ እሰድዳለሁ" የሚለውን አምላካዊ ቃል ኪዳን አሰበ፡፡

ክርስቲያኖች በቤተክርስቲያን ተሰብስበው ስለ እርሱ እየጸለዩ ነው፡፡ ጴጥሮስ ደግሞ በእስር ቤት ሆኖ "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝ የለም" በማለት ራሱን ለማያንቀላፋው የእስራኤል ጠባቂ አደራ ሰጥቶ እርሱ አንቀላፋ፡፡ በቤተክርስቲያን የነበሩት ግን ስለጴጥሮስ ከመጸለይ አላቆሙም፡፡ "ጌታሆይ ጴጥሮስን ፍታውና ወደ እኛ መልሰው" እያሉ ወደ እግዚአብሔር እየጮሁ ነበር፡፡ ድንገትም በእስር ቤቱ ሰማያዊ ብርሃን ሞላ፡፡ የጌታ መልአክም ወደ ጴጥሮስ ቀረበ፡፡ ጴጥሮስን "ፈጥነህ ተነሣ" አለው፡፡ ጴጥሮስ የታሰረባቸው ሰንሰለቶች ከእጁ እየወለቁ ወደቁ፡፡ መልአኩም "ልብስህን ልበስና ተከተለኝ" አለው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም መልአኩን ተከተለው፡፡ የእስር ቤቱን ጠባቂ ዘበኞቹን አልፈው መዝጊያውም አውቆ ተከፍቶላቸው ወጡ፡፡ መልአኩ ጴጥሮስን እየመራ ደቀመዛሙርቱ ወዳሉበት አመጣው፡፡



www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ለጸሎታችን ምላሽ ይሰጣል፡፡ በአብያተ ክርስቲያናቱ ስለ ጴጥሮስ ለተጸለየው ጸሎት እግዚአብሔር ምላሽ ስለሰጠ መልአኩን ላከ፡፡ መልአኩም ጴጥሮስን ከእስር ቤት ነጻ አወጣው፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ቅዱስ ጴጥሮስን ያሳሰረው ንጉሥ ማን ነበር?
2. ጴጥሮስ ሲታሰር በቤተ ክርስቲያን ምን ተደረገለት?
3. እግዚአብሔር ጴጥሮስን እንዴት ከእስር ቤት አወጣው?

## ተግባራት

- መምህሩ ልጆቹን እግዚአብሔርን “መላእክትህ በዙሪያችን ከብበው እንዲጠብቁን ስላደረግህልን እናመሰግንሃለን” ብለው እንዲያመሰግኑት ያድርግ፡፡
- ልጆች የመላእክትን ሥዕል እንዲሥሉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# እናትና አባትን ማክበር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ወላጆቻቸውን እንዲያከብሩ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አባትህንና እናትህን አክብር" ዘፀ. ፳÷፲፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ኤፌ. ፮÷፩ እና ዘዳ. ፭÷፲፮

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ወላጆቻችሁን ታከብራላችሁ?
- ልጆች ወላጆቻችሁ ምን ያህል እንደሚወዷችሁ ታውቃላችሁ?
- ልጆች አባትና እናት ማለት ምን ማለት ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አባት ማለት የወለደ፤ አልብሶ አብልቶ አጠጥቶ በሥርዓት አስተምሮ ተከባክቦ ያሳደገ፤ በሥጋና በመንፈስ የአባትነትን ሥራ የፈጸመ ማለት ነው፡፡ እናት ማለት አምጣ የወለደች፣ ተንከባክባና መግባ ያሳደገች፤ በሥጋና በመንፈስ የእናትነትን ሥራ የፈጸመች ማለት ነው፡፡

ልጆች አባትና እናትን ማክበር ከዐሥርቱ ትእዛዛት አንዱ ትእዛዝ ነው፡፡ ኦሪት "እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ላይ ዕድሜህ እንዲረዝምና መልካም እንዲሆንልህ" ትላለች፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ "ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና" ይላል፡፡ አባትና እናትን ማክበር የተስፋ ቃል ያላት የፊተኛይቱና የኋለኛይቱ (የአዲሲቱ ቃልኪዳን) ትእዛዝ ነው፡፡ አባትና እናቱን የሚያከብር እግዚአብሔርን ያከብራል፤ አባትና እናቱን ሳያከብር እግዚአብሔርን አከብራለሁ ማለት ግን አይችልም፡፡

ልጆች ዮሴፍ ለምን እንደተባረከ ታውቃላችሁ? ዮሴፍ ለአባቱና ለእናቱ ይታዘዝ የነበረ ተወዳጅ ልጅ ስለነበረ ነው፡፡ ልጆች በሥጋ ለወለዱን ወላጆቻችን፣ በመንፈስ ላሳደጉን አባቶቻችንና አረጋውያንን ማክበርና መታዘዝ አለብን፡፡ ይህን ካደረግን እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜና በረከት ይሰጠናል፡፡

ልጆች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእናቱ ለቅድስት ማርያም ይታዘዝ፤ የባሕርይ አባቱን አብን ያከብር እንደነበር ታውቃላችሁ? የእርሱ ልጆች እኛም ወላጆችን በማክበር ልንመስለው ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

እናትና አባትን ማክበር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ነው፡፡ ልጆች እናትና አባትን በማክበር ረጅም ዕድሜ ማግኘት ይቻላል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. እናትና አባትን ማክበር ከማን ተማርን?
2. እናትና አባትን ለምን እናከብራለን?
3. ዮሴፍ ወላጆቹን በማክበሩ ምን ሆነ?

## ተግባር

መምህሩ ልጆች ዐሥርቱ ትእዛዛትን በጋራ እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የእግዚአብሔር ፍቅር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እንዲሁ የተወደድንበትን ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ፍቅር ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡” ፩ዮሐ. ፬÷፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሚል. ፩÷፪፣ ዮሐ. ፫÷፲፮ እና ፩ዮሐ. ፫÷፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እግዚአብሔር ምናችሁ ነው?
- ፍቅር ምንድን ነው?
- እናታችሁ ምን ያህል እንደምትወዳችሁ ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር ከእናት ፍቅር በላይ በሆነ ጥልቅ ፍቅር እንደሚወዳችሁስ ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር ግርማው የሚያስፈራ ሁሉን ማድረግ የሚችል ኃያል አምላክ ነው፡፡ እኛን ልጆቹን ግን በፍቅሩ ስቦ በፊቱ አኖረን፡፡ ልጆቹ ተብለን እንድንጠራ አንዲያ ልጁን እስከመስጠት ድረስ ወደደን፡፡

ልጆች እግዚአብሔር ስለ ሃብታችን ስለ ውበታችንና ስለ ዕውቀታችን በአጠቃላይ የእኛ በሆነ ነገር ላይ ተመሥርቶ ሳይሆን እንዲሁ ያለ ቅድመ ሁኔታ ነው የወደደን፡፡ እኛ በምክንያት እርሱ ግን ያለ ምክንያት ወደደን፡፡

እግዚአብሔር የወደደን በዘላለማዊ ፍቅር ነው፡፡ የሰው ፍቅር በጊዜ ይወሰናል፤ በሁኔታ ይመሠረታል፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ግን ጊዜ አይወስነውም፤ በሁኔታዎች አይመሠረትም፡፡ በዘርና በቀለም አይከለልም፡፡

ልጆች እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለወደደን እኛም ልንወደው ይገባል፡፡ እግዚአብሔርን መውደዳችንን ደግሞ ሕጉን በመጠበቅ እናስመሰክራለን፡፡ እርሱ ራሱ “ብትወዱኝስ ትእዛዜን ጠብቁ” እንዳለን፡፡

ልጆች አባታችን እንደሚያስብልን፤ እግዚአብሔር ከአባታችን በላይ ያስብልናል፡፡ ሌሊት ስንተኛ ይጠብቀናል፡፡ ቀን ክፉ ነገር እንዳይጎዳን ሞገስ ይሆነናል፡፡ እናታችን ከምትራራልን በላይ እግዚአብሔር ይራራልናል፡፡

www.zeorthodox.org

ልጆች የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ያሳድገናል፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ሁኔታዎች ሲለወጡ አይለወጥም፡፡

የእግዚአብሔር ፍቅር በሰው ማንነት አይመሠረትም፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ፍጥረቱን ይወዳል፡፡ እግዚአብሔርን ይወዱ የነበሩ ብዙ ደጋግ አባቶች አሉ፡፡ አብርሃም፣ ዳዊት፣ ኢዮብ፣ ኤልያስ፣ ዮሐንስ፣ ጴጥሮስና ሌሎችም ቅዱሳን እግዚአብሔርን ከልባቸው አጥብቀው ይወዱት ነበር፡፡ ስለ ፍቅሩ ዓለምን ንቀውት፤ ስለ ፍቅሩ ሞትን ደፈሩ፤ እርሱም በፍቅሩ ጠብቆ መንግሥቱን አወረሳቸው፡፡ ልጆች እኛም እግዚአብሔርን መውደዳችንን ለመግለጽ እርሱን ብቻ ልናመልክ፣ትእዛዛቱን ልናከብር፣ ስሙን በከንቱ ከመጥራት እንደበታችንን ልንገታ፣ የሰንበትን ቀን ልናከብርና ሌሎቹን ልንወድ ይገባል፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው፡፡ ፍቅሩ በሁኔታዎች ላይ አይመሠረትም፡፡ ፍቅሩ በጊዜና በሰው ዘር አይገደብም፡፡ ፍቅሩ ለሕዝብ ሁሉ ያለ ዳርቻ የሚፈስ ነው፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. እግዚአብሔር ለምን ወደደን?
2. እግዚአብሔር እንዴት ይወደናል?
3. እግዚአብሔርን መውደዳችንን በምን እንገልጣለን?

## ተግባር

- መምህሩ ለልጆቹ የወላጆችን ፍቅር መሠረት በማድረግ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ይንገራቸው፡፡
- ለፍቅሩ ምላሽ በዘመናቸው ሁሉ ምስጋና እንዲያቀርቡ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# መታዘዝ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በመታዘዝ የሚገኘውን በረከት ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ” ቆላ. ፫÷፳

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ኤፌ. ፮÷፩ እና ዕብ. ፲፪÷፭-፲፪

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ለወላጆቻችሁ ትታዘዛላችሁ?
- ስለ ታዛዡ ይስሐቅ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች መታዘዝ ትልቅ በረከት ያስገኛል፡፡ መታዘዝ ከሰነፍ መሥዋዕት ይበልጣል፡፡ መታዘዛችን እግዚአብሔርን ያስደስተዋል፡፡ ወላጆችን ማክበርና መታዘዝ ያሳድጋል ዕድሜን ያረዝማል፡፡

ይስሐቅ የሚባል ደግ ልጅ ነበረ፡፡ አባቱ አብርሃም በአንድ ወቅት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሊያቀርበው ጠየቀው፡፡ ይስሐቅም አባቱን እሺ ብሎ ታዞ ወደ ሞርያ ተራራ ወጣ፡፡ አባቱንም “ጎልማሳ ነኝና እንዳልጎዳህ እጄንና እግሬን እሰር” አለው፡፡ አብርሃምም ልጁ እንዳዘዘው አደረገ፡፡ ይስሐቅ እስከሞት ድረስ ለአባቱ ስለታዘዘ እግዚአብሔር ከሞት አዳነው፤ ረጅም ዕድሜና ባለጠግነትን ሰጠው፡፡ ልጆች ለወላጆች መታዘዝ እንዲህ በረከትን ያስገኛል፡፡

በአንድ ወቅት ዮሐንስ ሐፂር የሚባል ወጣት ነበር፡፡ በዐሥራ ስምንት ዓመቱ መንኩሶ ገዳማዊ ኑሮን ጀመረ፡፡ ልጆች መነኩሴ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?

ዮሐንስ ለገዳማውያኑ የሚታዘዝ በጎ ወጣት ነበር፡፡ አበምኔቱ ለዮሐንስ ደረቅ እንጨት ሰጠውና “ተክለህ አለምልመው” አሉት፡፡ ዮሐንስም “እሺ አባቴ” ብሎ ደረቁን እንጨት ተከለ በየቀኑ ሁለት ጊዜ ሳይሰለች ውኃ ያጠጣው ነበር፡፡ ለረጅም ጊዜ ሳያቋርጥ ደረቁን እንጨት በየቀኑ ውኃ ያጠጣው ነበር፡፡ ዮሐንስ ሐፂር የገዳሙ አበምኔት ያዘዘውን በትሕትና በመፈጸሙ እግዚአብሔር ጥረቱን መልካም ሥራውን ባረከለት፡፡ ደረቁ እንጨት ለመለመ፤ ሰፋፊ ቅጠሎችን አወጣ ፍሬም አፈራ፡፡ ዮሐንስ ሐፂር ለአበምኔቱና ለመነኮሳቱ ፍሬውን አሳያቸው የመነኮሳቱም አበምኔት “ልጄ ሆይ ይህ የመታዘዝህ ፍሬ ነው” አሉት፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ወላጆቻችንን ከእኛ ይልቅ ትልቆችና አስተዋዮች ናቸውና ስንታዘዛቸው በረከትና መልካም ነገሮችን እናገኛለን፡፡ በደስታ በትሕትና ብንታዘዛቸው እግዚአብሔር የመታዘዝን ፍሬ ያበላናል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ልጆች ወላጆቻችንን በመታዘዝ የምናገኘው ጥቅም ምንድን ነው?
2. ወላጆቻቸውን የማይታዘዙ ልጆችን እግዚአብሔር ይወዳልን?
3. የመታዘዝን ፍሬ ያዩ ሁለቱ ወጣቶች እነማን ነበሩ?

## ተግባራት

- መምህሩ ልጆች ወላጆቻቸውን ሊያግዙ የሚችሉበትን መንገድ ያስተምራቸው፡፡
- የዮሐንስ ሐፂርን ታሪክ አንድ ሕፃን እንዲተርክ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ታማኝ መሆን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ስለ ታማኝነት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአት እሠራለሁ" ዘፍ. ፴፱÷፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሮሜ. ፫÷፫ እና ቆሮ. ፭÷፮

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ከወላጆቻችሁ ተደብቃችሁ የማይፈልጉትን ክፉ ነገር አድርጋችሁ ታውቃላችሁ?
- ልጆች ሰው ዋሽቷችሁ ያውቃል? ምን ተሰማችሁ?
- ስለ ታማኝነት የምታውቁትን ለወላጆቻችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ዮሴፍ የሚባል አንድ ወጣት ነበር፡፡ ወንድሞቹ ሸጠውት በግብጽ አገር በጲጥፋራ ቤት በሠራተኛነት ተቀጠረ፡፡ ጲጥፋራ ዮሴፍን ወደደውና በብዙ ሃብቱ ላይ ሾመው፡፡ ዮሴፍ በአንድ ወቅት ትልቅ ፈተና ገጠመው፤ ይህ ፈተና ታማኝነቱ የሚለካበት ነበር፡፡

ጲጥፋራ በቤት አልነበረም፡፡ የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን "ኃጢአት እንሥራ ጌታዬ የለም" አለችው፡፡ ዮሴፍ ግን "ጲጥፋራ ባይኖርም ታማኝነታችንን መተው የለብንም" አላት፡፡ እርስዋም መልሳ "የሚያየን ሰው የለም ለጲጥፋራ ማንም አይነግረውም" አለችው፡፡ ዮሴፍ ግን "ሰው ባያየንም እግዚአብሔር ያየናል እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት እሠራለሁ?" አላት፡፡ ዮሴፍ ኃጢአት ባለማድረጉ ለእግዚአብሔርም ለጲጥፋራም ታማኝ ሆነ፡፡

ልጆች ሰው ቢያየንም ባያየንም ያልተፈቀደልንን መንካት፣ የእኛ ያልሆነውን መውሰድ፣ መዋሸትና ማጭበርበር የለብንም፡፡ ወላጆቻችን ባያዩንም፤ እግዚአብሔር ያየናል፤ የእግዚአብሔር ዓይኖች በሥፍራ ሁሉ ናቸውና፡፡ ምሳ. ፲፭÷፫፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ታማኝነት ያስከብራል፤ ያሾማል፤ ያሸልማል፤ በረከትንም ያስገኛል፡፡ ታማኞችን እግዚአብሔርም ሰዎችም ይወዷቸዋል፡፡ ታማኝ መሆን ውሸታም ከመሆን ያድናል፡፡ ታማኝ መሆን መልካም ሥራ እንድንሠራ ያደርገናል፡፡

### ጥያቄዎች

1. የታማኞች አርአያ ማን ነው?
2. ታማኝ መሆን ለምን ይጠቅማል?
3. ሰው ባያየን ማን ያየናል?

## ተግባር

መምህሩ በልጆች ዕለታዊ እንቅስቃሴዎች ታማኝነታቸውን የሚለኩ አጋጣሚዎችን በመንገር ሁልጊዜ ታማኝ እንዲሆኑ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ማክበር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ለልጆች በማስተማር በአግባብ እንዲመላለሱ ማብቃት

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጿቸው" ፩ተሰ. ፫÷፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ተሰሎንቄ. ፫÷፯-፲ እና ዮሐ. ፪÷፲፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?
- በቤተ ክርስቲያን ማድረግ የሌለብንን ነገሮች ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ አምልኮ የሚከናወንበት ቅድስት ቤት ናት፡፡ እግዚአብሔር ልጆቹን የሚጎበኝባት ሥፍራ ናት፡፡ እግዚአብሔር ወደ ቤቱ በደስታ የሚመጡትን በበረከት ይጎበኛቸዋል፡፡ ልጆች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ ሲሉን በደስታ መምጣት አለብን፡፡

ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊት ዓለም በመሆኗ መንፈሳዊ ሥርዓት አላት፡፡ ሥርዓተ አምልኮዋ በጸጥታ ስለሚከናወን የሥጋዊውን ዓለም ወሬና ጫጫታ አታስተናግድም፡፡ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ስለሆነች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ታከናውናለች፡፡

እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ ነው፡፡ ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን የሚከናወኑ ነገሮች ሁሉ በሥርዓት እንዲከናወኑ፤ አማኞችም በሥርዓትና በአግባብ እንዲመላለሱ ይፈልጋል፡፡

በአንድ ወቅት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤተመቅደስ ሲገባ በውስጥ የነበሩት ቤተ ክርስቲያንን እንደ ንግድ ቦታ የሸቀጥ ገበያ አድርገውት፤ ሥርዓቱን ሳያከብሩ ስላገኛቸው በጣም አዘነ፡፡ ጅራፍ አበጅቶ በጎችን፤ በሬዎችንም ከመቅደስ እየገረፈ አወጣቸው፡፡ ርግብ ሻጪዎችንም ተቆጣ "የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጓት" ብሎ አባረራቸው፡፡ ልጆች ቤተክርስቲያን የጸሎት ቤት ናት፡፡ ሥጋዊ ነገር ማከናወን አይፈቀድም፡፡ እግዚአብሔር በሞገስና በጥበብ በፊቱ እንዲያሳድገን የቤቱን ሥርዓት ማክበር አለብን፡፡

በብሉይ ኪዳን በመሳፍንቱ ዘመን ሳሙኤል የሚባል ሕፃን ነበረ፤ ይህ ሕፃን የመቅደሱን ሥርዓት ያከብር እግዚአብሔርንም



www.zeorthodox.org

ይፈራ ነበር፡፡ አፍኒንና ፊንሐስ ደግሞ ሥርዓተ አልበኞች፤ ባለጌዎች ነበሩ፡፡ እግዚአብሔር ሳሙኤልን ለበለጠ ክብር አጨው፡፡ ሥርዓቱን ያላከበሩትን አፍኒንና ፊንሐስን ግን በሞት ቀጣቸው፡፡ ልጆች የቤቱን ሕግ የማያከብሩትን እግዚአብሔር ይቀጣል፡፡

## ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊት ዓለም ስለሆነች መንፈሳዊ ሥርዓት አላት፡፡ ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጡ ሁሉ ሥርዓቷን ሊያከብሩላት ይገባል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ሥርዓት አላት?
2. የቤቱን ሕግና ሥርዓት ለሚያከብሩ ልጆች እግዚአብሔር ምን ያደርግላቸዋል?
3. የእግዚአብሔርን ቤት ሕግ ባለማክበራቸው የተቀሰፉት እነማን ናቸው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ተግባራዊ ሥርዓት የሚለማመዱበትን መንገድ ያመቻች፡፡ ነጠላ አለባበስ፣ የማማተብ ሥርዓትና ሌሎችንም ያስታውሳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ቁርባንን መቀበል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆችን ስለ ቅዱስ ቁርባን በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" ዮሐ. ፮÷፶፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፮÷፵፰-፶፱፣ ማቴ.፳፮÷፳፮-፴ እና ፩ቆሮ. ፲፩÷፳-፴፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ቅዱስ ቁርባን ተቀብላችሁ ታውቃላችሁ?
- ልጆች ቅዱስ ቁርባን ከመቀበላችሁ በፊት ማድረግ የሚገባችሁ ዝግጅት ምንድን ነው?
- ልጆች ቅዱስ ቁርባን መቀበል የምንችለው የት ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ልጆች ሰው ሥጋና ነፍስ አለው፡፡ በቤታችን የምንበላቸው ምግቦችና የምንጠጣቸው መጠጦች ለሥጋችን መኖር ይጠቅማሉ፡፡ ነፍስ ደግሞ ለረሐቧ ማስታገሻ ምግብ ትፈልጋለች፡፡ የነፍስ ምግብ የእግዚአብሔር ቃልና ቅዱስ ቁርባን ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ክፉና ደጉን የሚያሳውቅ የጽድቅ ቃል ነው፡፡ ቅዱስ ቁርባን ደግሞ ክፉውን ዓለም ለማሸነፍ፣ በመልካም ሥራ ለመትጋት፣ ዲያብሎስን ድል ለማድረግና ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ለማድረግ ይጠቅመናል፡፡

ልጆች እስራኤላውያን በበረሓ ሲጓዙ ምን ይመገቡ እንደነበር ታውቃላችሁ? ከሰማይ የወረደ መና ይበሉ ከዐለትም የመነጨ ውኃ ይጠጡ ነበር፡፡ እኛም ወደ ሰማያዊት አገራችን በምናደርገው ጉዞ ከሰማይ የወረደውን የክርስቶስን ክቡር ሥጋ እንበላለን፤ ቅዱስ ደሙንም እንጠጣለን፡፡

ልጆች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር "እኔ ከሰማይ የወረድኩ ሕያው እንጀራ ነኝ፡፡ ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፡፡ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፡፡" በማለት አስተምሯል፡፡ ቅዱስ ቁርባን ስንቀበል ይህን አምላካዊ ቃል እየፈጸምን ነው፡፡

ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ሰውነታችንን ታጥበን፣ ነጠላችንንና፣ የታጠበ ልብሳችንን ለብሰን ወደ ቤተክርስቲያን እንመጣለን፡፡ ቅዳሴ አስቀድሰን ቁርባን እንቀበላለን፡፡ ይህን በማድረጋችን እግዚአብሔር ያሳድገናል፤ የዘላለም ሕይወት እናገኛለን፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ቁርባን የነፍስ ምግብ ነው፡፡ ቅዱስ ቁርባንን የሚቀበሉ ልጆችን እግዚአብሔር በቅድስና ያሳድጋቸዋል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ልጆች የነፍስ ምግብ ምንድን ነው?
2. ቅዱስ ቁርባን መቀበላችን ለምን ይጠቅመናል?
3. ቅዱስ ቁርባን ተቀበሉ ብሎ ያዘዘን ማን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች በሰንበተ ክርስቲያን ፕሮግራም ወጥቶላቸው በተራ እንዲቆርቡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# በጸሎት ማደግ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች የጸሎት ሕይወትን እንዲለማመዱ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሳታቋርጡ ጸልዩ" ፩ተሰ. ፭፥፲፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፮፥፱፣ ፊልጵ.፬፥፮ እና ፩ዮሐ. ፭፥፲፬-፲፭

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ምግብ ቀርቦላችሁ ከመመገባችሁ በፊት ጸሎት ታደርጋላችሁ?
- ስለ ጸሎት የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን ግንኙነት መሠረት ነው፡፡ ጸሎት ዲያብሎስን የምንዋጋበት ትልቅ መሣሪያ ነው፡፡ ጸሎት መልካሙ እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ሁሉ እንዲጠብቀን እርዳታ የምንጠይቅበት አንደበትና የምንግባባበት ቃል ነው፡፡

ልጆች እግዚአብሔርን ማናገር ፈልጋችሁ ታውቃላችሁ? ጸሎት አባታችንን እግዚአብሔርን የምናነጋግርበት ስልክ ነው፡፡

ሳሙኤል እየጸለየ በመቅደስ በማደጉ እግዚአብሔር ባረከው፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው የሚጸልዩ ልጆችን እግዚአብሔር ይባርካል፡፡ ዳዊት ገና ልጅ እያለ ጀምሮ ጣቶቹ እንኳ ሳይጠነክሩ በገና ይደረድር ነበር፡፡ በጸሎት ስላደገ እግዚአብሔር ባረከውና ንጉሥ አደረገው፡፡ ልጆች ወደፊት ትልቅ ባለማዕረግ መሆን ትፈልጋላችሁ? በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ካደጋችሁ ይሆንላችኋል፡፡

ጸሎት ምስጋና ነው፡፡ ልጆች እግዚአብሔርን በማመስገን ማደግ አለብን፡፡ ጸሎት የአምልኮ ክፍል ነው፡፡ እግዚአብሔርን በማወቅና በማምለክ ማደግ አለብን፡፡ ልጆች እንዴት መጸለይ እንዳለብን የተማርነውን ትምህርት ታስታውሳላችሁ? ምንስ እያልን እንጸልያለን? ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስትጸልዩም "በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን" በሉ አለን፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ልጆች እግዚአብሔር ከክፉ ጠብቆ እንዲያሳድገን ሳናቋርጥ መጸለይ አለብን፡፡

### ጥያቄዎች

1. ጸሎት ምንድን ነው?
2. ልጆች እንዴት መጸለይ አለብን?
3. ልጆች በጸሎት በማደጋቸው ምን ይጠቀማሉ?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች በተግባር እንዲጸልዩ ያድርግ፤ አቡነ ዘበሰማያትና በሰላመ ገብርኤል የሚባሉ ጸሎቶችንም ያስለምዳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ዋቢ መጻሕፍት


- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም።
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ኅሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም


www.zeorthodox.org

- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም፡፡
- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.
- በጠቅላይ ቤተ ክህነት፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ የኢትዮ. ኦርቶ.ተዋ. ቤ.ክ ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም፡፡ አዲስ አበባ ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር )፡፡ 2000፡፡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡
- ጎርጎርዮስ(ብፁዕ አቡነ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡
- መሐሪ ትርፌ (በሊቀ ሊቃውንት)፡፡ 19 ዓ.ም፡፡ የጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ዳንኤል ተሾመ፡፡ 19 ዓ.ም፡፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ስልቶች፡፡ አ.አ
- Pulpet ; 19 A.D; Bible commentary The Epistle of paul to the ROMAN;
- Tadros Yakob Malaty (Father); 2007-2008 A.D; The Epistle of Saint Paul to the Romans; Alexandria,Egypt.
- መብራቱ ኪሮስ (ዲያቆን)፡፡ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡፡ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያልታተመ መማሪያ፡፡

www.zeorthodox.org

- ጎርጎርዮስ (በብፁዕ አቡነ):: 1981 ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ:: አዲስ አበባ::
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር ):: 2001:: የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ 1ኛ እና 2ኛ:: አዲስ አበባ::
- Lule Melaku (Asst. Professor); 2010; History of the Ethi. Orthodox Tewahido Church; A.A ; Elleni p.p.plc.
- ሰሎሞን መላኩ(ዲያቆን):: 2001ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት:: አዲስ አበባ:: ባናዊ ማተሚያ::
- Syrian Sunday school curriculum.
- Introduction to Coptic orthodox Church ; Father Tadros Y Malaty
- Ian Gillman,Hans-Joachim Klimkeit ; Christian in asia before 1500 ;
- ዜና ሐዋርያት
- ገድለ ቅድስት አርሴማ
- ሺኖዳ(ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ) ቅንዓት
- የኢትዮፕያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ ፤ ስንክሳር ፤ በትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ
- ያረጋል አበጋዝ (ዲ/ን):: ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ ፤ አዲስ አበባ
- በጌታቸው ኃይሌ(ፕሮፌሰር):: 1997 ዓ.ም:: የአባ ባሕርይ ድርሰቶች
- ዳንኤል ክብረት(ዲ/ን):: 1998ዓ.ም:: የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች:: አዲስ አበባ:: ሜጋ ማተሚያ ቤት::
- .........:: አዋልድ መጻሕፍት:: ሐመረ ተዋሕዶ::
- Douglas J.D and Tenney M.c (1987) New International BIBLE DICTIONARY. ZONDERVAN'S.Grand Rapids,MICHIGAN USA
- Holy Trinity College.(2004) Patrology: Holy Trinity College module/ unpublished./
- Malaty T.Y( Father)Patrology ;
- Malaty T.Y( Father).(199). Tradition and Orthodoxy. Alexandria .Egypt.


www.zeorthodox.org

- ማኅበረ ቅዱሳን። 2004 ዓ.ም። ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ። አዲስ አበባ። የማዕረግ ቃል ማተሚያ ቤት።
- ነገረ ማርያም
- Shenoda - Pope (1999). The Holy virgin Saint Mary. Cairo,Egypt.
- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት። (1988) ወንጌል ቅዱስ ትርጓሜ። አዲስ አበባ። ብሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
- የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት መማሪያ ፤ ካናዳ
- ሺኖዳ ሰው ምንድነው ፤ በብጹዕ ወቅዱስ ፤
- ክርስቲያን አንትሮፖሎጂ
- ሺኖዳ (ብጹዕ ወቅዱስ ፤ አቡነ)። መንፈሳዊው ሰው
- John Mark (Father). 19 . Ascending the heights ; A lay man guide to the ladder of divine ascent
- አበራ (በሊቀ ጉባዔ ፤ አባ)። 1996 ዓ.ም። ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት። አዲስ አበባ። ማኅበረ ቅዱሳን።
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)። 200 ዓ.ም። መሸከርመምና ማሸከርመም። በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ። አዲስ አበባ
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)። 2000 ዓ.ም። ቅድመ ጋብቻ። በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ። አዲስ አበባ
- ተስፋ ገብረ ሥላሴ። 1988። መጽሐፍተ መነኮሳት። አዲስ አበባ
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት።
- ጥዑመ ልሳን።() ያሬድና ዜማው። አዲስ አበባ።
- ሙሳ (ሊቀ ጳጳስ)። ወጣትነትና የቅድስና ኑሮ። በመምህር ወንድወሰን ሶርሳ የተተረጎመ።

www.zeorthodox.org